


የመለስ
ልቃቂት
ኤርምያስ ለገሰ
P.⑤F 400-450

አንድ፡ የከባድ መኪናና ሎኮሞቲቭ ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

ሁለት፡ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

ሦስት፡ የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽንና ተከላ ቢዝነስ ዩኒት

አራት፡ የአውቶሞቲቭ የእርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

እነዚህን አደረጃጀቶች በመጠቀም መስፍን ኢንዱስትሪያል አሁን እያመረታቸው ካሉት የፋብሪካ ምርቶች ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ አመታዊ ሽያጭ የማከናወን ደረጃ ላይ ደርሷል። ኩባንያው በአሁን ወቅት እያመረታቸው ካለው መካከል የደረቅና ፈሳሽ ጭነት ማጓጓዣ ተሳቢዎች፣ ሃይቤድ እና ሎውቤድ፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዲፖዎች፣ ለሲሚንቶ ፋብሪካ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ አገልግሎት የሚውሉ ፔንስቶክር ኢትዩብ ላይነር... ወዘተ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ የኤሌክትሮ መካኒካል ተከላ ስራዎች፣ ለተለያዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ የማሽን ተከላ ስራዎች፣ የሲቪል ሀንጻ ግንባታዎች፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ቀለበቶች፣ ፕሮጀክቶችን ከጅምር እስከ ፍጻሜ በማሰራት ላይ ይገኛል።

በመቀሌ 100 ሔክታር ላይ የሚያርፈው እና ከ15 በላይ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን የሚያቅፈው የመስፍን ኢንጂነሪንግ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ መንደር ግንባታ ሲጠናቀቅ የብረታ ብረት ማቅለጫ፣ የንፋስ ተርባይኖች፣ የክሬን፣ የአውቶብሶችና የባቡር ፉርጎዎች ማምረቻዎች ይኖሩታል። በተመሳሳይ መንገድ በወቅሮ ከተማ በ50ሺህ ካሬ ሜትር ላይ እየተገነባ ባለው የመስፍን ኢንዱስትሪያል መንደር የቤት አውቶሞቢሎች፣ ሚኒባሶችና ፒካፕ ተሽከርካሪዎች ይመረታሉ። እነዚህ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች ሲጠናቀቁ የመስፍን ኢንዱስትሪያል አቅም በእጥፍ እጥፍ የሚያድግ ሲሆን፣ የሚፈጥረው የስራ እድል አሁን ካለበት 2500 ወደ 10ሺህ የሚያድግ ይሆናል።

***

የካቲት 24 ቀን 2015

ሁለተኛ ቀጠሮ

ስርአቱ በቃኝ ብለ ወደ አሜሪካን ከተሰደደቻቸው ካድሬ ጓደኞቹ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኝተናል። ለደት የኢትዮጵያውያን እጣ ፋንታ በመሆኑ በየመንገዳችን የምናየው ኢትዮጵያዊ

ስፍር ቁጥር የለውም። እጅግ በጣም ጥቂቶች (በተለይ አዛውንት እናትና አባቶች) እጃቸውን መልክ ስላለን ብቻ ሰላምታ ይሰጡናል። አብዛኛው ግን አይቶ እንዳላየ አሊያም ሰላምታ ሰላምታም ተጠይፎ ጥርቅም አድርጎን ያልፋል። ዘግየት ብዬ እንደሰማሁት በሀገረ አሜሪካ ለረጅም አመታት የኖረውና አዲስ ስደተኛ ለመለየት ከሚያገለግለው አንዱ "የእግዜር ሰላምታ ነው። ከመንገደኛው ውስጥ የአንተን ሰላምታ የሚያቀርበው ለአገሩ ባዕዳ የሆነው አዲስ ስደተኛ ነው። የሚያስጨንቅ ፊት አሳይቶ አሊያም አይቶ እንዳላየ ከሚሄደው ውስጥ አብዛኛው ረጅም ዓመታት ያደረገው ነው። ከወጣቶች ውስጥ ፀጉሩን በቅባት አብለጭልጮ ፍሪዝ ያደረገ፣ ቤት ከአዱገነት የቢሮ ፀሀፊ በተስተካከለ ሁኔታ ዝንጥ ያለች ከሆንች እሱ/እሷ የኢትዮጵያ ከውስጣቸው ገና ወጥቶ አላለቀም። አትብታቸው የተቀበረበትን ቀዬም ገና አልረሱም።

ከማይከፈልበት የእግዜር ሰላምታ ባሻገር የስደት ምክንያቶችም የስደተኛውን ስብዕና የሚወስኑበት ጊዜ አለ። ስደተኛው ከአገር ቤት ጀምሮ አሁን እስከደረሰበት ድረስ ያሳለፈው መከራና ውጣ ውረድ፣ በፖለቲካ ምክንያት ያጋጠሙት አስጨናቂ ሁኔታዎች፣ ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመቅረፍ አላማ አድርጎ የሚካሄድ ሩጫና ጥድፊያ የባህሪ ለውጥን የመለካት ጉልበት አላቸው። ይህም ሆኖ ከአብዛኛው ሐበሻ የሚወጡ ተመሳሳይ ማጽናኛ ቃላቶች አሉ። "አይዞህ ትለምደዋለህ። ሲስተም ውስጥ እስከትገባ ነው!"

ከሁሉም ቀሎ የተመለከትኩት በፖለቲካ ውስጥ (በስርአቱ ደጋፊዎች ሆነ ተጠቃሚዎች) የሚሳተፉትን ሰዎች በሚያሳዩት ጣባይ መለየት መቻሌ ነው። አብዛኞዎቹ የህወሓት/ኢህአዴግ አባላት የበግ ለምድ የለበሱ ናቸው። እንደበታቸውን ርዕቱ ለማድረግ ይሞክራሉ። ተጨማሪ ማይል የሔደ ደግነት ለማሳየት ይጥራሉ። ይቅለሰለሳሉ። በተቻለ መጠን በምክንያታዊነት ለመናገር ጥረት ያደርጋሉ። ከህወሓት አባላት በስተቀር በምንም ተአምር የህወሓት ኢህአዴግ አባል መሆናቸውን አይናገሩም። የፓርቲውን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎች ቢያውቁ እንኳን ጋጋርታማ ናቸው። ከእነዚህ በተቃራኒ የተቃዋሚው ጎራ በስርአቱ ላይ ያለውን ተቃውሞ ለመግለጽ የሚፈራ እና የሚሸሸግ አይደለም። እንደበታቸው በውስጣቸው ያለውን እምነት ለመግለጽ የሚቆጠብ አይደለም። በተለይ የስርአቱ ዘረኝነት የተገለጠላቸው ሰዎች በተገኙበት ቦታ ሁሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገን ለማሰማትና ለመቃወም የሚሰሱቱት ጉልበት የላቸውም። በራስ መተማመናቸውን ከርቀት ማየት ይቻላል። ታዲያ በዚህ ጎራ ያሉትን የተቃዋሚ አመራሮች እና አባላት አንድ ወዳጄ ከፍ ካለ መሰላል ላይ ካለ ሰው ጋር ያመሳስላቸዋል። በተለይ አመራሩ። መሰላሉ የቆመበት መሬት

በር በርካታ ሹል ምስማሮች ተሰክተዋል። የተቃዋሚ መሪዎች መሰላሉ ማዶ ላይ ከቆሙ በኋላ ህዝቡን የእሳት ወላፈን በማንባር ቀደምትነት ማስተጋባት ካልቻሉ መሰላሉ በሾሉ ይመታሉ። ማረፊያቸውም ሹል ምስማሮች ይሆናሉ። እጥንት የሌለው ፍጡር ይሆን ገራ እንዲቀላቀል አይመከርም። "የስደት መቀመጫ" ላይ አርፎ ቢቀመጥ ይሻለዋል።

እነሆ! ይህን የመሳሰሉ ወጎች ለካድሬዋ ጓደኛዬ እያጫወትኳት ጊዜው ነጎደ። እሷም አገር ቤት ወስዶ መለስ እያደረገች ብዙ ቁምነገሮች አጫወተችኝ። በመጀመሪያው ማስታወሻዬ ላይ ("መለስ ትሩፋት") የተጠቀሱ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ካሉበት ሁኔታ የምታስታውሰውን ነቅሳ በማውጣት አጫወተችኝ። ከኢትዮጵያ ለመሰደድ ምክንያት የሆናት "የአዲስ አበባ ኦሮሚያ ማስተር ፕላን የጋራ ኮሚቴ" አባል በመሆኗ የተመለከተችው የህወሓት አደገኛ አካሄድ መሆኑን ጨምራ ነገረችኝ። "በመለስ ትሩፋት" ላይ የተጠቀሱት ሁነቶች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች የጋራ ኮሚቴውን (በተለይም የኦሮሚያ ተወካዮችን) ለሁለት እየከፈለ እንዳጫቃጨቀ ገለጠችልኝ።

በማስታወሻዬ ላይ የተጠቀሱ የቀድሞ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ ያሉበት የተለያየ ደረጃ ስለ ለውጥ በተማሪ ቤት የተማርኩትን አስታወሰኝ። ስርአቱ ላይቀየር ሰዎች ሊለወጡ ይችላሉ። እነሱ የተለወጡት ረግቶ የሻገተውን ስርአት ማነቃነቅ ባለመቻላቸው ነው። አንዳንዶቹ የውስጥ አርበኛ በመሆን ስርአቱን ለመቦርቦር እየሞከሩ ቢሆንም በሚፈለገው ፍጥነት እና የአጣዳፊነት ስሜት በመፍጠር (Sense of Urgency) መጓዝ አልጀመሩም። በመተማመን ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የለውጥ ሀይል መፍጠር አልቻሉም። ከህወሓት ውጭ በመካከለኛ እና ዝቅተኛ እርከን ላይ ያሉት የኢህአዴግ ካድሬዎች በስርአቱ ቢማረሩም ድፍረት የላቸውም። በቋሚነት የሚመጣው ስርአት እንዳይተፋቸው በመፍራት ሙሉ እጃቸውን በለውጡ ላይ አላስገቡም። ይህም ሆኖ ከመታሰር፣ ከስራ ከመባረርና ከመሰደድ አያመልጡ አይደለም። አንዳንዶቹም እየተሙለጨለጩ በስልጣን እርከን ላይ ቀጥለዋል። ሚኒስትር፣ አምባሳደርና ከንቲባ የሆኑም አሉ። በሚያሳዝን ህይወት ውስጥ የሚገኙም ብዙ ናቸው። ከህወሓት ቅርቃር ውስጥ መውጣት ከባድ ነው። በአንድ በኩል ማር መቅመስ አለ፣ በሌላ በኩል ዘወትር ረፍት የማይሰጥ ሀሲና አለ። እስቲ አንዳንዶቹን እንያቸው።

ከበረሃ ጀምሮ አብሮአቸው የመጣው የጉራጌ ካድሬው ካሚል አህመድ ነብሱ በአማር እጅ ወድቃለች። ያ! ጠረጴዛ የሚደበድብ እጅ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሐይለማርያምን፣ ያ[illegible] ሚኒስትር መኩሪያ ሃይሉን፣ ሚኒስትር ሬድዋንን የመለመለ፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ያስተማረ ቱጭ ብድግ ያደረገ እንደበት ወደ ፍፃሜው እያመራ ነው። አንድ ተቃዋሚ በገባበት ምርጫ 2002 ብቸኛ የኢህአዴግ ተሸናፊ ካሚል አህመድ እንዲሆን ተደርጓል። ካሚል ከኢህአዴግ ፖለቲካ ባሻገር በማር ማላስ ውስጥ በሰፊው መንንዳጎድ መጀመሩ ተሰምቷል። በየጊዜው ቻይና አፍሪ ደም ለማስቀየር እጅ ማርጠብ ግድ ይላል። አሊያም ህወሓት ሆኖ መፈጠር።

ዘብጥያ የወረዱም ብዙ ናቸው። ከአማራ ክልል መጥቶ የነበረውና እን በረከትን አፍንጫችሁን ባሱ በማለት ከአርከበ እቁባይ ጋር የተጣበቀው ምትኩ ሀበን ቃሲቴ ወርዷል። ምትኩ አሁንም እሳፍር ብሎ የመለስ ሙት አመት፣ የካቲ ፲፩ ግንቦት 20 በአላትን ለመሰብ ወንድም!" በመባል የሚታማው የቂርቆስ ክንቲባ ሲሳይ እያሴው ታስሯል። (በክንራትን ሴ የትውልድ አካባቢውም እነጋገሩም ቁርጥ ልደቱ ነው።) የቅርብ ጓደኛዩ እና የድራዳዋ ምክትል ከንቲባ የነበረው ሲሳይ ዝምድናውን አይቀበልም። ገና የልደቱ ስም ሲነሳ ያንገሸግሸዋል። ጁነዲን ሳዶ ከእስር አምልጦ ወደ አሜሪካ ተሰዷል። ጁነዲን በአትላንታ የሚኖር ሲሆን በአቶ መለስ በረከት ላይ ያለው ጥላቻ የትየለሌ እንደሆነ የቀረቡት ሰዎች ይገልጣሉ። ጁነዲን በሀይወት ቢኖርም የኦህዴድ ባለስልጣናት የነበሩት አለማየሁ አቶምሳና አሊ ሲራጅ የአሎላክ ገሪ ደርሶአቸዋል። (ጎረቤት ለነበረው አለማየሁ አቶምሳ ጥንቃቄ እንዲያደርግ በመጀመሪያው ማስታወሻ ላይ መገለጡ ልብ ይሏል።) የኦህዴድ ካድሬዎች እየተለቀሙ ዘብጥያ መውረዳቸው በተጠናከረ ሁኔታ ቀጥሏል። በምርጫ 97 ማግስት ከአባዱላ ጋር እየዞረ በአዲስ አበበ ዙሪ ችካልና ቢልቦርድ ሲያስተክል፣ የተቃውሞ የመዲናይቱን ነዋሪዎች ሲያሳስር የነበረው ዘላለም ጀማነህ እግረ መቅ ሲጠለቅለት እንደሚችል የውስጥ አርበኞች ነግረውናል።

የአባ ዛላለም አሳሪ ደግሞ ትላንትና "የአዲስ አበባ ህዝብ ቅንጅትን እንደመረጠ፣ ቅንጅት ያድነው" በማለት አብሮት የተናገረው ፍቃዱ መሆኑ በራሱ አስገራሚ ነው። ፍቃዱ ዛሬ ተገልብጦ ለሚኒስትር ጥላን ሲናገር መስማት የምራል ለኩቱን የሚያመላክት ነው። ትላንት "የአሮሞ መሬት በትግራይ ሰዎች ተወረረ" እንዳላለ ዛሬ ተከርብቶ የኦሮሞን ህዝብ ሲያስጨፈጭፍ ማየት ይዘገንናል።

በአጭር ጊዜ የውርደት ካባ የተከናነቡ ጓደኞቼም ብዙ ናቸው። "በፖለቲካ ምክንያት ለዚህም የተሰደደ ጋዜጠኛ የለም" በሚለው ዘመን ተሻጋሪ ንግግሩ የሚታወቀው ሽመልስ ከማል በሰው ጅብ አልፎጭህም ብሏል። ከኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት በካልቾ የተመታው ሬድዋን ሁሴን በወራሩ በዓት ስቴዲየም እየተገኘ እግር ኳስ አስጀማሪ ሆኗል። እንደሰማሁት ቀልደኛ ካድሬዎች ሬድዋንን መ'ራብ መደበኛ ስራቸው አድርገውታል። ከእለታት በአንዱ ቀን ስቴድየም የክብር እንግዳ ሆኖ፤ በክብር ትሪቪዩን ተቀምጦ ኳስ ይመለከታል። ጨዋታው የቡና እና ደደቢት ነበር። በመጀመሪያው ኢጋማሽ አንዱ የቡና ተጨዋቾች ጉዳት ደርሶበት ሜዳ ላይ ይወድቃል። ሬድዋን አጠገቡ የተቀመጠውን የስፖርት ጋዜጠኛ ጠርቶ "ዜግነቱ ሳይረጋገጥ መጎዳቱ በኢቲቪ እንዳይገለጽ!" አለ አሉ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ አንድ የደደቢት ተጨዋቾች ተመሳሳይ ጉዳት ደርሶበት መሬት ላይ ይዘረራል። ይህን የተመለከተው ሬድዋን ሜዳ ገብቼ ተጫዋቾቹን ህክምና ካልሰጠሁ በማለት ለዖዥ ገናኝ አስቸገረ አሉ።

ወደ ቁምነገሩ ስንመለስ "በመለስ ትሩፋት" ውስጥ ከተጠቀሱት ባለስልጣናት ተጨማሪ ስልጣን የተሰጣቸው አሉ። እነዚህ ሰዎች አብዛኛዎቹ ከበረሃ የመጡ ታጋዮች ናቸው። በተለይ የህወሐት ታጋዮች በስልጣን ላይ ስልጣን ተጨምሮላቸዋል። የካሳንቹሱ መንግስት ጥቁር እንቁ የነበረችው ተጋዳሊት ፈትለወርቅ (ሞንጆሪኖ) ገ/እግዚአብሔር የባላንጣዋን አዜብ መስፍን ስልጣን የተካች ይመስላል። ትግራይ ድረስ በመሄድ ህዝቡን እስከ መሳደብ ደርሳለች። ህዝቡ በቅሬታ ተቆጥቦ እንዲቀመጥ አስፈራርታለች።

`በምርጫ 97 "አንድ የቅንጅት አባል በጥይት በርቅሼ ስገድል ነው የምረጋጋው" እያለ ሲፎከር የነበረው ታጋይ ነጋ በርሄ ከመቀሌ ተዘዋውሮ በሚኒስትር ደመቀ መኮንን የሚመራውን የኢህአዴግ ቢሮ ተቀላቅሏል። ምክ/ጠ/ሚኒስትር ደመቀ መኮንንን በኮምፒውተር ድንቁ ዜሮ እና አንድም ላይ የሚያደርገው እሱ ሆኗል። ነጋ የኢህአዴግን ቢሮ (የአዲስ አበባን ጨምሮ) መዳፉ በቁጥጥር ስር አውሏል። ...ታጋይ ተወልደ የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ክንፍ ሊቀመንበር ሆኗል።... የልጆቹን ስም አስተካክሎ መፃፍ የማይቻለው ኢኮኖሚስቱ ታጋይ ይሳቅ አበራ (ቁራጥ) ተንከረባብቶ በሚኒስትር ዲኤታ ማዕረግ የመድን ዋስትና ዋና ዳይሬክተር ሆኗል። ካድሬዎቹ ጓደኞቹ የይሳቅ ቁራጥን ሹመት ስትነግረኝ ሳላስበው በመገረም በሆቴሉ የሚጠጡም ሰዎች እየዞሩ ተመለከተውኝ ነበር። ...በምርጫ 97 ላፍቶ ለተገደሉት ወጣቶች ቀጥተኛ ትዕዛዝ እንደሰጠ

የሚታወቀው ሐይሌ ፍሰሃ አዲስ አበባ በባለቤትነት ተስጥታዋለች። የአርከበ እቁባይ የቢጋ ዘመዲ የሆነው ሐይሌ ፍሰሃ የአዲስ አበባ ዋና ስራስኪያጅ በመሆን በመሬት ላይ እንደፈለገ እንዲያዝ ባለሙሉ ስልጣን ሆኗል። አርከበ እቁባይ በእጅ አዙር የአዲስ አበባን ከንቲባነት እንዲያገ ፈጥሮለታል። ...በምርጫ ፺፯ አዲስ አበባን ከአርከበ ጋር በመሆን "ወዳልደረቀ አፀም የዋየሩት አዲሷ ህወሓቱ ዶ/ር አብርሃም የኢኮኖሚና የፋይናንስ ሚኒስትር ዲኢታ ሆኗል። የፌደራል መንግስቱ የደምስር የሆነው ፋይናንስ ባልተለመደ ሁኔታ በቀጥታ በህወሓቶች ስር (ቀድሞ በተዘዋዋሪ ነበር) እንዲወድቅ ተደርጓል።... የቦሌ ከፍለከተማ ወደ አንድ የትግራይ ዞንነት የመቀየር ጉዳይ የተጠናቀቀ ይመስላል። ለተራዘመ ጊዜ ከንቲባ የነበረው የህወሓት አባል ዮሐንስ ይባላል።

የቦሌ መሬት ላይ እንዲወስን የመሬት አስተዳደር ሀላፊ የሆነው ደግሞ ታጋይ ሻለቃ ፍቃዱ በጦርነት በደረሰበት ጉዳት ከመከላከያ ተዘዋውሮ ቦሌ እንዲመደብ የተደረገ ነው። ከሰባተኛ ክፍል በላይ መዝለል ያልቻለው ፍቃዱ ወ/አረጋይ የሰማይ ላይ ካርታ ማንበብ የሚጠይቅበት ማስተር ፕላን አንብቦ መረዳት ግድ የሚልበት እና መሰረታዊ የኢንጂነሪንግ እውቀት የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ ለመሾም አላገደውም። የህወሓት መሆን በራሱ በቂ ነው። ...የኢህአዴግ የፕሮፖጋንዳ ከፍልም መልሶ በታጋዮችና ህወሓት አመራሮች ቁጥጥር ስር ገብቷል።... ከመቀሌ ዩኒቨርስቲ በመጥፎ ስነ ምግባር (ውጤት ለማስተካከል ከተማሪ ገንዘብ በመቀበል፣ ከአሙቱ የስራ ቀን ግማሹን በስራ ገበታ ላይ ባለመገኘት፣ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ጫት እየቃሙ በመገኘት፣ ግሬድ ለማስተካከል ወሲባዊ ጥያቄ በማቅረብ፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር ላይ የማድያ ማስፈራሪያ በማቅረብ፣ በስብዕና የመጥፎ ሰው ምሳሌ በመሆን (በዩኒቨርሲቲ ቋንቋ "ቦረከ" ይባላል) በመሳሰሉት ምክንያቶች) የተባረረው ጌታቸው ረዳ የፕሮፖጋንዳ ማሽን የበላይ ሀላፊ እንዲሆን ተደርጓል።... ምክትሉ የአዲስ አበባ ከንፍ አባልና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ ዋና አዘጋጂ ተጋዳሊት ፍሬህይወት ሆናለች። ወይዘሪት ፍሬህይወት በጌታቸው ልክ "ጆሴፍ ጎብልስን" ስላላነበበች የፕሮፖጋንዳ ማሽኑ አያሌው ከብዷታል። ... ሌሎች የፕሮፖጋንዳ ማሽኑ ማስተጋቢያዎች ኢቲቪ፣ ኢዜአ፣ ሬዲዮ ፋና፣ ዋልታ እና ፈቃድ ሰጪው ብሮድካስቲንግ ኤጀንሲ የበላይ ሃላፊዎች በሙሉ የህወሓት ታጋዮች ሆነዋል። ብርሃነ ማዕረት፣ ዘርአይ አስግዶም፣ ወልዱ ይመስል፣ ሀዱሽና ገ/ሚካኤል ስለ ኢትዮጵያ የገድታ ግንባታ የሚጨነቁልን ናቸው። የገድታ ግንባታው በድምጽ ብቻ ሳይሆን በቴሌቭዥንም እንዲደገፍ በመወሰኑ ዋልታና ፋና ቅድመ ዝግጅት በአንድ አመት ውስጥ እንዲያደርጉ አቅጣጫ ተቀምጧል። ኢዜአ፣ ኢቲቪ እና ፐሬስ ክፍል በእጃቸው የሚገኘውን የማማሽ ከፍለዘመን ቪዲዮና ዶክመንቴሽን ኮፒ አድርገው በነጻ እንዲሰጡ አብዮታዊ መመሪያ ተላልፏል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ

የህወሓት ኩባንያዎች የሆኑት ሬዲዮ ፋና እና ዋልታ ኢንፎርሜሽን ሲቋቋሙ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ከኢህአዴግ ቢሮ በደረሰው ብጣሽ ወረቀት በአንድ ወር ውስጥ ያሉትን ዶክመንቴሽኖች ኮፒ በማድረግ በነፃ አስረክቧል። አቶ መለስ በመጽሐፉ "እነዚህ ተቋማት ከመንግስት የተደረገላቸው ቅንጣት ታክል ድጋፍ የለም። ሰባራ ሳንቲም አልወሰዱም" ቢልም ዋልታና ፋና በነፃ የወሰዱት መረጃ 25 ሚሊዮን ብር ያህል የሚገመት ነው። አንዳንዶቹም የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ቋሚ ቅርስ የሆኑ ለሌላ ሳይተላለፉ በሙዚየም መቀመጥ የሚገባቸው ነበሩ።

ከኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ተሞክሮ የተቀሰሙበት "ክላስተሪንግ" አሰራር ህወሓትን በሚፈይ መልኩ ጠቅሞታል። ህዝቡና ፖለቲከኛው ወከልነው ከሚሉት ህዝብ ቁጥር በማነፃፀር የሚኒስትር ብዛታቸውን ሲኮንን የፈጠረባቸውን መሸማቀቅ "የአቀራረብ ማሻሻያ" በማድረግ ከድሮው በበለጠ በቁጥጥር ስር አውለውታል። የኢኮኖሚና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክላስተር ፀሳፊ የሆነው ታጋይ ደብረጺዮን የግብርና ሚኒስቴር፣ የፋይናንስ ሚኒስቴር፣ የመገናኛ ሚኒስቴር፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ የመረጃ እና ደህንነት ኤጀንሲ (ኤንሳ)፣ ቴሌኮሚዩኒኬሽን… ወዘተ ተጠያቂነት ለእሱ እንዲሆን ተደርጓል። የተዘረዘሩትን ተቋማት የሚመሩት ሚኒስትሮች ደብረጽዮንን ተሻግረው ሐይሌማሪያም ደሳለኝ ጋር መድረስ አይችሉም። የክላስተሪንግ ህግ ተሻግሮ መሔድ አይፈቅድም። የፀጥታና ደህንነት ክፍል ("ክላስተር") የበላይ ሃላፊዎቹ አባይ ፀሃዬና አለቃ ፀጋዬ የሀገሪቱን የሰላም፣ የመከላከያና ፖሊስ ክፍል፣ የክልሎች የፀጥታ ቢሮ፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ተጠያቂነት በራሳቸው ስር አድርገዋል። የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ለአባይና አለቃ ፀጋዬ የስራ መመሪያ የመቀበልና ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል። ሐይለማሪያም እንደ ኢኮኖሚ ክላስተሩ ሁሉ የፀጥታና ደህንነቱ ጉዳይ የሚያሳስበው አይደለም። የውጭ ጉዳዩም ቢሆን ሃይሌን የሚያስጨንቀው አይደለም። አጠገቡ የተቀመጠው ሚኒስትር ብርሃነ ገ/ክርስቶስና ሚኒስትር ቴዎድሮስ አድሃኖም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩን ("ገዞና- ስዩም")፣ የአምባሳደርና ዲፕሎማት ምደባን፣ ከውጭ ሀገራት ጋር የሚኖረው ግኑኝነት የሚያቅዱና የሚወስኑ ናቸው። እርግጥ ነው የውጭ እንግዳ "እንኳን ደህና መጣህ… የኢትዮጵያ ቆይታህ አስደሳች እንደሚሆን አረጋግጥልሃለሁ!… መልካም መንገድ ይሁንልህ!" ለማለት ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ የሚያሳፍር አይደለም። ቻይኒኛም ይችላሉ።

(በነገራችን ላይ የፎርቹን ጋዜጣ ገለቤት ታምራት ገገርርኒስ ሐይለማሪያም ደሳለኝን በጋዜጠኞች ፊት "በስልጣን ላይ ያለው ማነው?" የሚለው ጥያቄ ከመጀመሪያው ማስታወሻ ዉሃ ከተመቹኝ ጥያቄዎች አንዱ ነው። ታምራት ከበረከት ስምኦን ጋር ባለው ቅርበት የተነሳ ጥያቄው በእጅ አዙር ከበረከት የቀረበ እንደሆነ ቢጠረጠርም በራሱ ብዙ የሚለው ነገር አለ። በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ለመንግስት ቅርበት ያለው የድረ-ገጽ ሚዲያ የአዲስ አበባ ህዝብ ጋር በመዞርና ናሙና በመውሰድ "የኢትዮጵያ የአሁኑ ፕሬዝዳንት ማን ይባላል? የአዲስ አበባ ከንቲባ ሙሉ ስሙ ማነው?" ለሚለው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ እጅግ በጣም ብዙ ነገር ይነግረናል።)

ካድሬዳዋ ጓደኛዬ ጋር የነበረን ቆይታ ሊጠናቀቅ ሲል የማትረሳቸው ትዝታዎች የትኛዎቹ እንደሆኑ ጠየኳት። እቶ መለስ በፃፈው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት ፖሊሲዎች" ላይ ስልጠናዎች የወሰዱት ጊዜና አሰልቺነቱ እንደማይረሳት ነገረችኝ። እሷ እስከነገረችኝ ድረስ የስልጠናውን ርዝማኔ በፍጹም ያሰብኩት አልነበረም። እርግጥም በአንድ አመት ውስጥ ከሚኖረው የስራ ጊዜ ሲድስት ወር ያህሉን የምናጠፋው በኢንዶክትሪኔሽን የካድሬ ስልጠና ነው። አዳማ (ሁለት ወር)፣ አላጌ (ሁለት ወር)፣ ሲቪል ሰርቪስ (ሁለት ወር)፣ ሰንዳፋ (ሁለት ወር)… በአንድ አመት ውስጥ!! …ታዲያ ይሔ ሁሉ ጊዜ በኢንዶክትሪኔሽን ጠፍቶ የመጣ ለውጥ የለም። ለውጥ አልባ ኢንዶክትሪኔሽን!

እስከገባኝ ደረስ በየጊዜው የሚካሄዱት ስልጠናዎች ለውጥ የማያመጡ ከሆነ በይዘቱ ላይ ችግር አለ ማለት ነው። ካድሬዎች በማያምኑበት አሊያም ከነባራዊ እውነት ጋር ሊዛመድላቸው ባልቻለ ጉዳይ ላይ የባለስልጣናት እና የካድሬዎች የጭንቅላት ደረጃ የማይመጣጠንበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም ውጤቱ ባዶ ይሆናል። ካድሬዋ ጓደኛዬም የምታነሳልኝ ይህንኑ ነው። እርግጥም ስለ ግሎባላይዜሽን እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) የአፋሩን ፕሬዝዳንት እሲሲሮንና የገዛብ ሚኒስትሩ ሱፊያን አህመድ አንድ መቀመጫ ላይ አስቀመጦ ማሰልጠን ምን የሚሉት ነው? ስለ "ኪራይ ሰብሳቢነት" (Rent Seeking) የኢኮኖሚክስ ትርጉም ለመስጠት ለአምባሳደር ግርማ ብሩና የትግራይ ፕሬዝዳንት አባይ ወልዱ ስልጠና ሲሰጥ ምን ማለት ነው? …እማርኛ ማንበብ የማይችሉት የሱማሊያ፣ ጋንቤላ፣ አፋር፣ ትግራይ…ወዘተ ካድሬዎችን 'የግጠርና ግብርና፣ የአቅም በላይ የሆኑ መጽሐፎችን አሸክሞ ለወራት በአዳራሽ ውስጥ መጎለት ምን የሚሉት ነው?…

ከድሬዎ ጓደኛዬ ጋር ቆይታ አድርጌ ወደቤቴ ስመለስ ብዙ ነገሮች ወደ ኋላ ሔጄ እንዳስታውስ አደረጉኝ፤ የወጣትነት እድሜዬን የበላው በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥርዓትም መደቆስንና ማደቆስን መሆኑ ገረመኝ። ለወራት መደቆስ፣ ለመንፈቅ ማደቆስ፣ በጣም ያሳዝናል። የባከኑ ዘመናት፣ አይደማ ለኪን "አንድ አጥር በመሬት"፣ "ተሞክሮዎችንና ጠባብነትን፣ ተሞክሮ ዚራይ ሰብሳቢ"፣ አብዮታዊና ኒዮሊብራል"፣ "ተሰፈኛና የሚያሸፍ (ጥንጋፍ) መምህራንን"፣ ያልተቀለለ ዳቦና ሳንጠራራ የምናወርደው ፍሬ"፣ "ከውጭ ወደ ውስጥ እና ከውስጥ ወደ ውጭ"፣ "አሮጊቷና አዲሲቷ ኢትዮጵያ"፣ "ቆረጣና መሳሰጫ"፣ "ሂስ ግለሂስ" መምጣትና አለመምጣት፣ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ"፣ "አካሄድ ኢንጂነሪንግ"… እረ ስንቱ!

ነገርን ነገር ያነሳዋል እና እነዚህ የፖሊሲ ሰነዶች በአቶ መለስ ተጽፈው በአገር ደረጃ ይተገበራሉ ይባላል እንጂ አተገባበሩ ከቦታ ቦታ ይለያያል። በተለይ በትግራይ ክልል ከኢንዱስትሪያላይዜሽን ይመራዋል የተባለው አፈርት ከእነዚህ ፖሊሲዎች በተቃራኒ የሚንቀሳቀስ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው አቶ መለስ የጻፈው "የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች" የሚለው ሰነድ ነው። በዚህ ፖሊሲ መሰረት የአገሪቱ ግብርና ልዩ ትኩረት የሚሰጠው የበሬ ማንባር የምታከለው የአርሶ አደር ማሳ፤ በዝናብ ላይ ያተከረ ግብርና፣ በሰው ጉልበት ላይ ያተከረ እርሻ እና ትንንሽ የውሃ ማቆሪዎች ላይ የተመሰረተ የመስኖ ስራ ነው። ከዚህ በተቃራኒ የኤፈርት ኩባንያ የሆነው ህይወት ሜካናይዜሽን በከፍተኛ የግብርና ደረጃ የአግሮኖሚ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም፣ ከፍተኛ ካፒታል የሚያፈስ (Capital intensive) እና በትላልቅ መስኖዎችና ሰፋፊ መሬቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ዘመናዊ የግብርና ስርአት ነው። ለዚህም ሲባል ቀድሞ በትግራይ ክልል አንዳልነበሩ የሰውና የደክመውን መረጃ የቀረበባቸው ከወንዝ ግዳ ያሉትን ሁመራ፣ ወልቃይትና ጠገዴን በጉልበት በመያዝ ሰፋፊ እርሻ እንዲኖር አድርገዋል። የኤፈርት ኩባንያ የሆነው ህይወት ሜካናይዝድ የሆነ እርሻ በማስፋፋት ዘመናዊ የሰለጠኑ ገበሬዎችን የመፍጠር ስትራቴጂ ይከተላል፤ በተቃራኒው አቶ መለስ ጽፎ ተግባራዊ የሆነው የግብርና ስትራቴጂ በሌሎች አካባቢዎች የገበሬን ልጅ ገበሬ ለማድረግ ይተጋል። በፖሊሲው ገፅ 48 ላይ ያስቀመጠው አቅጣጫ "ቀጣይነት ያለው አደር ትውልድ መፍጠር" ይላል። ህይወት ሜካናይዜሽን በዐሺዎች ሔክታር መሬት ላይ ለኤክስፖርት የሚሆኑ የቅባት እህሎች በዘመናዊ መንገድ ያመርታል፤ በተቃራኒው የቤንሻንጉል ጉሙዝንት የነበረው ያረጋል አይሸሹም ቤኒሻንጉል ለሜካናይዝድና ለትላልቅ መስኖ ስራ ተስማሚ እንደሆነች ስገልፅ ያሁሩን እናገና ብለውኛል።

የሚል ጥያቄ በማቅረቡ ከስራ ይባረራል። ለበብ ተፈልጎ ቃሊቲ ይገባል። ህይወት ሚሊዮን ብር የሚቆጥሩ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ገበሬዎችን ለመፍጠር ግብ ይንቀሳቀሳል፤ በተቃራኒው አቶ መለስ የሄፈውና በሌሎች አካባቢ ተግባራዊ የሆነው ፖሊሲ "ድሐን የበለጠ የሚያደህይት" ስትራቴጂ ይከተላል። እርግጥም በስልጣን ላይ መሰረታዊ ለውጥ በማያመጡ የቁጥ ቁጥ ስራዎች ላይ ማተኮር ለህዳጣኖች ትክክለኛ ነው። በቁጥ ቁጥ መስራት ከድህነት እንደማያወጣ ሳይታለም የተፈታ ነው። ድህነት ዜጋ ደግሞ ስለራሱ ያለው አመለካከትና ሞገስ ዝቅተኛ ነው። በድህነቱ ምክንያት ሊጎናፀፈው የሚገባውን መሰረታዊ መብቶች የመጠየቅ ድፍረት ያጣል። በዚህም ምክንያት አገዛዝ ስር የመቆየት እጣ ፋንታው የተራዘመ ይሆናል። ለዚህም ነው በረከት ስምኦን በመጽሐፉ "የእኛ አርሶአደር ተኛ ስንለው ይተኛልናል።... አርሶ አደሩ በእኛ ፍቅር ያበደ በማለት በድፍረት እስከመግለጥ ያደረሰው።

ለማንኛውም የግብርና ፖሊሲው እና ህይወት ሜካናይዜሽን በተቃራኒ እየተጓዙ በማስረጃ አስደግፎ መመልከቱ የተሻለ ስዕል ይሰጣል። በቅድሚያ በግብርና ፖሊሲው ላይ አንድ እግር መሬት እና "ሳንጠራራ የምናወርደው ፍሬ" የተባለውን በአጭሩ ተመልክተን ወደ ህይወት ሜካናይዜሽን አፈጣጠርና የእድገት ጉዞ እንመለሳለን።

***

"አንድ እግር በመሬት"

አቶ መለስ በመላው ኢትዮጵያ እንዲተገበር ያወጣው የግብርና ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከሚመራበት መሰረታዊ አቅጣጫዎች ውስጥ አንዱ "አንድ እግር በመሬት" መሆን በገጽ 35 ላይ፣

"ማንኛውም በፍጥነት ለመጓዝ የሚፈልግ ሰው እፈጥናለሁ ብሎ ሁለቱን እግሮቹን በአንድ ጊዜ በማንቀሳቀስ ሊራመድ ቢል ለአጭር ጊዜ መዝለል ይሆናል እንጂ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ጉዞ ሊኖረው አይችልም።በፍጥነት መጓዝ የሚቻለው አንድ እግርን መሬት ላይ በማድረግ ብቻ ነው። አንደኛው እግር መሬትን ሳይለቅ ከረገጠ በኋላ ሌላው ወደሚቀጥለው ለመሸጋገር በአየር ላይ ሲሆን፣ በአየር ላይ የነበረው አልፎ ሄዶ መሬት ሲረግጥ፣ መሬት ረግጦ የነበረው እየተነሳ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የእግር ጉዞ ማድረግ የሚቻለው። የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎች

ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ጉዞ ሊኖረው የሚችለው ተመሳሳይ አቅጣጫን በመከተል ብቻ ነው።" በማለት ይገልፃል።

ሌላው በፖሊሲው የተገለጠው የመስኖ ስራ ላይ ነው። የመስኖ ስራው በራሱ በአርሶ አደሩ የሚፈፀም እንደሆነ ያመላክታል። የውሀ ሀብትና መስኖ ስራ በቁጥቁጥ (በትንሽ በትንሹ) ያውም በተራዘመ ጊዜ እንደሚፈፀሙ ለማመላከት በገጽ 134 እና ገጽ 148 ላይ፤

"የውሀ ሀብት ልማትን ለማፋጠን በዋናኛነት በአርሶ አደሩ ማሳ ዙሪያና በራሱ በአርሶ አደሩ የሚከናወኑ በቀበሌ ደረጃ የሚሰሩ የመለስተኛ ግድብና ወንዝ ጠለፋ ስራዎችን ጨምሮ የተሟላና የተለያዩ የውሀ አጠቃቀም ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን አጣምረው የያዙ ፓኬጆች በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግና በየጊዜው ማሻሻል ያስፈልጋል።.. እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የምንከተላቸው የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች በተቻለ መጠን በዝቅተኛ ወጪ ሊሰሩ የሚችሉ እንዲሆን ማድረግና አፈጻጸሙም በተራዘመ ጊዜ በትንሽ በትንሹ እንዲሆን ማድረግ ነው።" በማለት ይገልጻል።

ከፍተኛ ካፒታል በውሀ ሀብት ልማት ላይ መጠቀም እንደሌለብን ለማሳየት በፖሊሲው ገፅ 106 ላይ፣

"የካፒታል ችግር ሲያጋጥም የሰው ጉልበት ካፒታልን ሊተካ በሚችልበት ደረጃ በሰፊው መጠቀም በሁሉም የልማት ስራዎቻችን የምንጠቀምበት መንገድ ነው። የውሀ ሀብታችንን በማልማትም ረገድ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ስለሚኖር ጉልበትን በሰፊው በሚጠቅም አኳኋን የውሀ ሀብታችንን የማልማት ስልትን ዋነኛው መፍትሄ አድርገን መውሰድ አለብን። አስተማማኝና ሰፊ የልማት ሀይላችን የሰው ሀይላችን ስለሆነ የውሀ ሀብታችንን በማልማት ስራም ላይ ያለብዙ የገንዘብ ወጪ በሰው ጉልበት ሊሰሩ በሚችሉ ስራዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለበት አገራችን ከፍተኛ ካፒታል በመጠቀም ላይ ያተኮረ የውሀ ሀብት ልማት አቅጣጫ መከተል አንችልም። ይህን አቅጣጫ ብንከተልም የውሀ ሀብት ልማት እንቅስቃሴያችንን በከፍተኛ ደረጃ ከማዳከም አልፎ የሚገኝ ጥቅም አይኖርም።" በማለት ይገልጻል።

"ሳንንጠራራ የምናወርደው ፍሬ"

በዚህ ርዕስ ስር የተቀመጠው ቁምነገር ተጠቃሎ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፤

"ከፍተኛ ፍሬ ያፈራ የዛፍ ፍሬ ከታች እስከላይ የበሰለ ፍሬ ይዞ ሲገኝ አወራረዱን ግራ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ መሰብሰብ ያለባቸው ፍሬዎች መሬት ላይ ሆነን ሳንጠራራ በቀላሉ ልንሰበስባቸው የምንችል ፍሬዎች መሆን ይገባቸዋል። እነዚህን ፍሬዎች በቀላሉ ከሰበሰብን በኋላ ከመሬት ራቅ ብሎ የበሰሉትን ፍሬዎች ወይ ዛፉ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ወጥተን መሰብሰብ ልንሻገር እንችላለን። ይህን አድካሚና ጊዜ የሚጠይቅ ስራ የምንሰራው በቀላሉ ሊሰበሰብ የሚችለውን ፍሬ ለቅመን ከጨረስን በኋላ መሆን ይገባዋል።...

"የግብርና ቴክኖሎጂን በተመሳሳይ መልኩ ልናየው እንችላለን። የአገሮች ቴክኖሎጂያችንን በላቀ ደረጃ አለም የደረሰበት የምርታማነት ደረጃ ላይ የማናደርስበት ምክንያት የለም። የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን በሂደት በመስኖ ሊለማ የሚችለውን መሬት ሁሉ በማ አልምተን በአመት ሶስቴ ከፍተኛ ምርት የማናገኝበት ምክንያት የለም። ይሁንና እዚህ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ጊዜ፣ ካፒታልና በላቀ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ይጠይቃናል። ከመሬት ራቅ ብሎ እንደሚገኝ የበሰለ ፍሬ ሊወሰድ ይችላል። ይህንን ፍሬ በመልቀም ስራ ላይ የምናተኩረው ሳንንጠራራ ልንለቅም የምንችለውን ፍሬ ለቅመን ከጨረስን በኋላ መሆን ይኖርበታል። መጀመሪያ የምንለቅመው ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ካፒታል፣ ጊዜና በላቀ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል የማይጠይቀውን ቴክኖሎጂ መሆን አለበት።...

"የተሻሻለ አግሮኖሚ ስንል አለም የደረሰበት የላቀውን ሳይሆን የኛ መሀይም ወይም በከፊል የተማረ አርሶ አደር ተግባራዊ ሊያደርገው የሚችለውን ነው። ስለሆነም በተግባር እና አሁኑኑ ሳንንጠራራ ልናወርደው የምንችለውን ቴክኖሎጂ መሆን አለበት። በመስኖ የሚለሙ መሬታችንን በሙሉ ለማልማት ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ታላላቅ ግድቦችን አሁኑኑ መገንባት ሳይሆን በጥቂት ገንዘብና በሰፊ ጉልበት ቢያንስ አንድ ጊዜ ጥሩ ምርት የምናመርትበትን መሬት የሚታረስ መሬታችንን፣ በዝናብ ውሀ ብቻ በአመት ሁለት ጊዜ ልናመርትበት የምንችልበትን በሚሊዮኖች ሄክታር የሚቆጠር ኮትቻ አፈራችንን፣ በመለስተኛ የወንዝ ጠለፋ ወይም በአነስተኛ የጉድጓድ ቁፋሮ በመስኖ ልናለማው የምንችለውን በሚሊዮኖች ሄክታር የሚቆጠር መሬታችንን ማልማት ሊሆን ይገባል። በተጨባጭ በኛ አቅም ሊሰራ የሚችል መሆኑንና መንገዳችን የማይጠይቅ መሆኑ ያረጋገጥነውን ቴክኖሎጂና ፍሬ ሳንሰበስብ ወደ መንጠራራት መሄድ የለብንም።...

"ትላላቅ ግድቦችን ለመስራት ምን ያህል ወጪ ማውጣት እንደሚያስፈልግ መገመት ይቻላል። በአሁኑ ወቅት በዚህ መልኩ የሚሰራ መስኖ ለማሰራት በሄክታር ቢያንስ 100 ሺህ ብር ይጠይቃል። አንድ ሚሊዮን ሄክታር በዚህ አኳኋን እናልማ ብንል 100 ቢሊዮን ብር ይጠይቃል። በመለስተኛ የወንዝ ጠለፋና አነስተኛና መካከለኛ ጥልቀት ያለው ጉድጓድን በመጠቀም ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ማልማት እንደሚችል የሚገመት ሲሆን በመስኖ ውሀ አጠቃቀም መስክ መንጠራራት ሳያስፈልገን የምናወርደው ቴክኖሎጂ ምርታችንን በስንት እጥፍ ሊጨምረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም።" በማለት ይገልጻል።

እንግዲህ ከእነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች መረዳት የሚቻለው ነገር አቶ መለስ የቀረፀው የግብርና ፖሊሲ ትኩረቱ በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ሲሆን የሚከናወነውም በራሱ ጉልበት ጥፍርና ቀንበር ጠምዶ ነው። የመስኖ ስራም ብዙ የማይበረታታ በተለይም ካፒታል የሚጠቀም ከሆነ ብክነት እንደሆነ የሚገልፁ ነው። በቲዎሪ ደረጃ ከላይ የተገለፀው ባልከፋ ነበር። አንዳንዶቹም ትርጉም የሚሰጡና የሚያከራክሩ ናቸው። ማንኛውም ሰው ባለው ነገር ላይ መሰረት አድርጎ ማቀድ አለበት። ጥያቄው ለምን በሁሉም ቦታ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ አይተገበርም ነው ፤ ሰዎች ስለ ሜካናይዜሽን እርሻ፣ ስለ መስኖ ስራ አስፈላጊነት ሲያነሱ ለምን የአቶ መለስ አይን ይጉረጠረጣል ነው። አንድ እጁን በሌላ እጁ እየጠበጠበ ለምን ይሳደባል? ለማንኛውም ይህንን በልቦናችን አሳድረን የትግራይ ካፒታሊዝም እንዲመራ ሀላፊነት የተሰጠው የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ህይወት ሜካናይዜሽን ምን አላማ አንግቦ፣ እንዴት እንደሚሰራ እንመልከት።

***

### "ህይወት የእርሻ ሜካናይዜሽን"

የትግራይ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ (ኤፈርት) ተቋቋመ ከመባሉ በፊት በህወሓት ታጋዮች አክሲዮን ባለቤትነት እንዲቋቋሙ ከተደረጉት ስትራቴጂክ የኢኮኖሚ ዘርፍ አንዱ ህይወት ሜካናይዜሽን ነው። ህይወት ሜካናይዜሽን ህወሓት በግብርናው የኢኮኖሚ ዘርፍ በዘመናዊ የማምረት ዘዴ ተጠቅሞና ትላልቅ የግብርና ፕሮጀክቶች ላይ አተኩሮ እንዲሰራ ታስቦ ተወስዶ የተመሰረተ ነው። ዘመናዊ የማምረት ዘዴው ሰፋፊ ለም መሬቶችን በመጠቀም፣ ትራክተርና ኮምባይነር ያሉ ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን በአገልግሎት ላይ በማዋልና ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ የመስኖ ግንባታዎች በማካሄድ እንዲፈፀም ታስቦ የተመሰረተ ኩባንያ ነው።

ህይወት ሚካናይዜሽን በመጀምሪያ የተመሰረተው በአምስት ነባር የህወሓት ታጋዮች (ሙ ነው። እነዚህም ቅዱሳን ነጋ፣ ገብርኤል ታደሰ፣ አርአያ ታፈሰ፣ አብርሃ ወልደና ግርማይ ገብሳሲ ናቸው። ቅዱሳን ነጋ የትግራይ ክልል ሴቶች ማህበር ሊቀመንበር፣ የስብሃት ነጋ እህትና የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው አሊቃ ፀጋዬ ሚስት ናት። እነዚህ መስራች አባላት እያንዳንዳቸው 25 ሚሊዮን ብር አዋጥተዋል በሚል የተመሰረተ ነው። ኩባንያው የገንዘብ አቅሙን ለማሳለበት በሌሎች የኤፈርት ኩባንያዎች የአክሲዮን ባለቤት ሆኗል። በዚህ መሰረት ህይወት የአክሲዮን ባለቤት ከሆኑባቸው የኤፈርት ድርጅቶች መካከል አፍሪካ ኢንሹራንስ፣ አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ መሰፍን ኢንዱስትሪያልና ተስፋ የእንስሳት ሃብት ልማት ይገኙበታል።

"ነሐሴ 14 ቀን 1987 ዓ.ም. በተካሒደ ስብሰባ ህይወትን የመሰረቱት የህወሓት ታጋቾች የአክሲዮን ድርሻቸውን ለትዕምት፣ አልመዳ፣ ጉና እና ተስፋ የእንስሳት ሀብት እንዲያስረክቡ ተደረገ። ይህን ውሳኔ ተከትሎ የህይወት ሚካናይዜሽን ባለቤቶች የኤፈርት ኩባንያዎች ሆኑ። የአክሲዮን መጠናቸውም በሰንጠረዥ ቁጥር 16 እንደሚታየው ተሸንሽኗ።

| ተ.ቁ | የአክሲዮን ባለቤቶች | የአክሲዮን መጠን | የአንድ አክሲዮን ዋጋ | ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትዕምት | 969,999 | 25.00 | 24,249,975.00 |
| 2 | አልመዳ ጨርቃጨርቅ | 10,000 | 25.00 | 250,000.00 |
| 3 | ጉና ትሬዲንግ | 10,000 | 25.00 | 250,000.00 |
| 4 | ተስፋ የእንስሳት ሃብት | 10,000 | 25.00 | 250,000.00 |

ሰንጠረዥ ቁጥር 16: የህይወት ሚካናይዜሽን አክሲዮን ባለቤቶች

ህይወት ሚካናይዜሽን በልዩ ትኩረት ሲቋቋም ሌሎች ተጨማሪ አላማዎች ነበሩት። ከእነዚህም ውስጥ የህወሓት ዲሞብ(ራ)ላይዝድ ታጋዮችን በሁመራ፣ ወልቃይትና ጠገዴ በማስፈርና የመሬት ባለቤት በማድረግ ቦታዎቹን በትግራይ ተወላጆች ሰብጥር (ዴሞግራፊ) መሙላት፣ ...ለኤፈርት ኢንዱስትሪ ዝርፍ ግብአት (ጥሬ እቃ) በማቅረብ እርስ በራስ የተሳሰረና

የሚመጋገብ ኢኮኖሚ መፍጠር፣... ህይወት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚቆጣጠራቸው ትላልቅና ዘመናዊ እርሻዎች ላይ በመስራት የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች መመስረት፣... ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ከፍተኛ ካፒታልን በመጠቀም ለኤክስፖርት የሚሆኑ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ብሎም ለትግራይ ህዝብ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ህይወት ሜካናይዜሽን ከላይ ከተቀመጡለት ስትራቴጂክ አላማዎች በተጨማሪ ሌሎች ስራዎችንም እንዲሰራ ግብ ተቀምጦለታል። ከእነዚህ መካከል ድርጅቱ የሚያመርታቸውን የቅባት እህሎች በጅምላና በችርቻሮ መሸጥ፣ ...ለሜካናይዜሽን እርሻ የሚያገለግሉ ትራክተሮችና ሌሎች ከባድ ማሽኖችን ከውጭ በማስመጣት መሸጥና ማከራየት፣ ...ከውጭ የሚገዙና ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎች ወኪል በመሆን ማስወጣት፣ ...በሌሎች የኤፈርት ኩባንያዎች ውስጥ በአክሲዮን አባልነት መሳተፍ።

የህይወት ሜካናይዜሽን የተግባር አፈፃፀም ስንመለከት ህወሓት ያስቀመጠውን አላማ በአጭር ጊዜ ማሳካት የቻለበት ነው። ቀድሞ በትግራይ ክልል እንዳልነበሩ የተረጋገጡትን ሁመራ፣ ወልቃይትና ጠገዴ በክልሉ ውስጥ በጉልበት እንዲገቡ በማድረጉ ሰፊ ለም መሬት ማግኘት አስችሎታል። ለጥጥና ሰሊጥ ማምረቻ ከ22ሺህ ሄክታር በላይ ወንዝ ተሻግሮ ማግኘት ችሏል። ይህን ያህል የተንጣለለ መሬት በማግኘት በመጀመሪያው ዙር ከህወሓት ታጋይነት የቀነሱትን 30ሺህ የትግራይ ተወላጆች በአካባቢው የማስፈር ሁኔታ ተፈጥሮለታል። በአጭር ጊዜ ውስጥ የአካባቢው ቋንቋና ዲሞግራፊ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። በሁለተኛና ሶስተኛ ዙር ታጋዮችን የመቀነስ ዘመቻ (በተለይ ሴት ታጋዮችን) በተመሳሳይ መንገድ አካባቢውን ለመውረር አግዟቸዋል። በነገራችን ላይ አንዳንድ የትግራይ ተወላጅ ፖለቲከኞች (የህወሓት ተቃዋሚዎችን ጨምሮ) ይሔ ኢፍትሐዊ እርምጃ እንደተወሰደ እያወቁ "ህዝብ ውሳኔ" የሚል መፍትሔ ሲያቀነቅኑ ይታያል።

ህይወት ሜካናይዜሽን ዘመናዊ የእርሻ ዘዴ የሚጠቀም በመሆኑ የትላልቅ ማሽነሪዎች ባለቤት ነው። የሰሊጥና ጥጥ ማምረቻው ክፍል ብቻ 120 ትራክተር እና 25 ኮምባይነሮች አሉት። ከዚህም በተጨማሪ ለጥጥ መዳመጫ የሚያገለግሉ በርካታ ማሽኖችን የያዘ ፋብሪካም በውስጡ ይገኛል። የህይወት ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ከአልመዳ ጨርቃጨርቅ ጋር ሊንኬጅ በመፍጠር አብሮ የሚሰራ ነው። ህይወት አገልግሎት ላይ የሚያውላቸው የግብርና መሳሪያዎች ከውስጥ አቅሙ ብቻ

የሚመነጩ አይደለም። በየጊዜው ከፌደራል መንግስቱ ውሃ ስራዎች ድርጅትና አዲስ አበባ እስት አይጋ የውሃ መቆፈሪያና ውሃ ማጠጫ ማሽኖች እና መኪኖች የውርስ አገልግሎት ፈጽሟል። ይሄ ተግባር በብዙ ሚዲያዎች በማስረጃ (ቪዲዮ) ተደግፎ የቀረበ በመሆኑ ሲስተባበል የሚችል አይደለም።

አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ሀይወት ሜካናይዜሽን የካፒታል ችግር የሌለበት ነው። በዚህም ምክንያት የሚጠቀማቸው የመስኖ ልማቶች በከፍተኛ ወጪ የተፈፀሙ ናቸው። በድርጅቱ ውስጥ ራሱን የቻለ "የመስኖ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ" በማቋቋም ለብቻ እንዲሰራ ተደርጓል። የመስኖ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ትላልቅ ወንዞችን በመጥለፍ ጭምር መስኖ የሚሰራ በመሆኑ በሙያው ልምድ ያላቸውን የውጭ ሀገር ኩባንያዎች በመጋበዝና በማጫረት የሚሰራ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው በዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልና ሪፖርተር ጋዜጣ በሐምሌ 09 ቀን 2002 ዓ.ም. የወጣው ዘገባ ነው። ዋልታ ባቀረበው ዘገባ መሰረት የመስኖ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ የእንገረብ እና ከዞ ወንዞችን በመጥለፍ ከ5ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በመስኖ ለማልማት የተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶችን ጋብዟል። ከድርጅቶቹ መካከል (United Kingdom Irrigation Company, Asaudi Irrigation Firm, Israeli Drip Irrigation Firm) ይገኙበታል።

የዘመናዊ የመስኖ አገልግሎት የቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ከአለም አቀፍ ተቋማት ከተካሔደ በኋላ ኤፈርት በራሱ አቅም ለመስራት ካቋቋማቸው ኩባንያዎች አንዱ "ብሩህ ተስፋ የመስኖና ውሃ ቴክኖሎጂ" ኩባንያ ነው። ብሩህ ተስፋ ወንዞችን በመጥለፍ የመስኖ ስራ ከመስራቱም በተጨማሪ የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችን በመስራት ከኤፈርት ኩባንያዎች አልፎ በመላ ሀገሪቱ በማስራጨት ላይ ይገኛል። በመሆኑም በተራዘመ ሂደት ህይወት ሜካናይዜሽን የመስኖ ስራ የሚያከናውነው በራሱ አቅምና መሳሪያዎች የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጥራል።

# ክፍል 3

# እውነት ወይስ አለሽ?

ምዕራፍ **12**

# ፈንጂ ወረዳ

*"ለስማው የማልወደውና ለማንዛቤዬ እንደ ስድብ ይቆጠራል ብዬ የምጠላው የሰዎች ዘርዝር "ማትግራይ ልማት በራስ-አገዝነትና ጥረት መለስ የተቀየሰ ነው" የሚለው ነው።"*

ሙሉጌታ ሉሌ (ጺጋዬ ገ/መድህን አርአያ)
ጦቢያ መጽሔት ቁጥር 8 1992 ዓ.ም.

***

ተደጋግሞ እንደተገለፀው በምርጫ 97 ማግስት ኢህአዴግ ቢሮ የተደራጁ ጊዜያዊ ቡድን በህዝቡ ውስጥ ቅሬታ የፈጠሩ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ጥናት አካሂዶ ነበር። ቡድኑ ካሠባሠባቸው የህዝብ ቅሬታዎች መካከል የአንበሳ ድርሻውን የያዘው በኤፈርት ኩባንያዎች ዙሪያ የተነሱት ነበሩ። ከህዝቡ ጋር በተለይም ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ነጋዴዎች ጋር የተደረገው የመድረክ ስብሰባ ውርጅብኝ ያስተናገዱት የኤፈርት ኩባንያዎች ናቸው። በወቅቱ በተጠሩት ከ[illegible] ሺህ በላይ የተማሪ፣ ነጋዴ፣ ነዋሪና የመንግስት ሠራተኛ መድረኮች በሚሊዮኖች ተገኝተው የህወሓት ድርጅቶች ላይ ያላቸው የመረረ ጥላቻ አሳይተዋል። እነዚህ የፓርቲ ኩባንያዎች የኢትዮጵያን ህዝብ በመዝረፍ ሞኖፖሊ መፍጠራቸው በመረጃ ተደግፎ ቀርቧል። ከህዝብ ተደብቆ የሚቀር ነገር የለምና በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት የኢትዮጵያ መንግስት የጦር መሳሪያና ተዋጊ አውሮፕላኖችን ለመግዛት ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ የተበደረው ከኤፈርት መሆኑ በህዝቡ ተገልጧል። "ይሔ እንዴት ሊሆን ይችላል?" በሚል ጥያቄ አፋጠውናል።

በመላው ሀገሪቱ በተጠሩት መድረኮች ህዝቡ በተለይም በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞች ኤፈርት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለአግባብ ማስያዣ ብድር እንደሚወስድ ዶክመንት እያገላበጡ ሞግተዋል። የኤፈርት ኩባንያዎች አልፎ በአልፎ በሆነ መንገድ የወሰዱትን ገንዘብ "የተበላሸ አካውንት" ውስጥ እንዲገባላቸው ተደርጎ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ምህረት

እንደተደረጉላቸው የባንክ ማስታወሻ እና የስርጭቱ ቅርብ የሆኑ የግል ሚዲያዎች እያጣቀሱ አቅርበዋል። ትዕምት በመከራ ጊዜ ለኢትዮጵያ መንግስት አበዳሪ በሆነበት ሁኔታ "እንዴት ብድሩ ይመልስለታል፣ ያለምንም መያዣ እንዴት የፈለገውን ያህል ብድር እንዲወስድ ተደረገ?" በማለት ማብራሪያ እንድንሰጣቸው ጠይቀዋል።

በመላው ኢትዮጵያ በተጠሩ ስብሰባዎች በተለይም የነጋዴዎች መድረክ የኤፈርት ኩባንያዎች የቦርድ አባላት፣ የዘርፍ ስራ አስፈጻሚዎችና አማካሪዎች የመንግስት ስልጣን የያዙ የህወሓት አመራሮች በሆኑበት ሁኔታ ነፃ ውድድር የማይቻል መሆኑን በምሳሌ በማስደገፍ አስረድተዋል። የገቢዎ፣ የኢንቨስትመንት እና መንግስት በኮንትራት ሊያሠራቸው የሚያስባቸው ትልልቅ የኮንትራት ፕሮጀክቶች መረጃ ገና ወረቀት ላይ ሳይሰፍር ለትዕምት ኩባንያዎች ስለሚደርሳቸው በአዲሲቷ ኢትዮጵያ "ልጅና የእንጀራ ልጅ ተፈጥሯል" በማለት አቅርበዋል። ለህወሓት ልጅ የሆነው ኤፈርት የኢትዮጵያ የንግድ ዋርካ ተደርገው የሚቆጠሩትን ነጋዴዎች እንዴት አድርጎ ከገበያ እንዳስወጣ በሠፊው ተነስቷል። የአሚልጋሜትድ ባለቤት የሆኑት ገብረየስ በኛ ላይ የተሰራው ወንጀል የመድረኩ ማጣፈጫ ሆኖ ነበር።

የትዕምት የቦርድ ሊ/መንበር የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሆኑበት፣ የቦርድ አባላት በሙሉ ታጋይ ባለስልጣናት በሆኑበት፣ የኩባንያው ዘርፎች(ኢንዱስትሪ፣ ማዕድን፣ ግብርና ማኑፋክቸሪንግ፣ ፋይናንስ፣ ንግድ) ዳሬክተሮች የህወሓት ቁልፍ አባላት በሆኑበት ሁኔታ እንዴት ገለልተኝነት ሊመጣ ይችላል በማለት ጠይቀዋል። ርግጥ የመንግስትን በቢሊዮን የሚቆጠር ቁልፍ ፕሮጀክቶች የሚነድፈው አቶ መለስ የስልጣን ዋስትናና ሐብቱን ሊያረጋግጥለት የሚችለውን ኤፈርት ከጭንቅላቱ ገሸሽ አድርጎ እንዴት ሊያቅድ ይችላል? የስልጣኑ ምንጭ የሆነውን የትግራይ ህዝብ በጠብታ ኢኮኖሚ ከሌላው በተለየ መጥቀም እንዳለበት የሚያምነውን እንዴት ሊያስቀር ይችላል? አሁን በህይወት ያሉት አቶ አርከበ እቁባይስ ቢሆኑ የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ግንባታ በበላይነት የሚያሽከረክሩበት፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ፋይናንስ ተቋማት የቦርድ ሠብሳቢ በሆኑበት፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን ለመምራት የፖሊሲ አውጭዎችና አማካሪዎች በሆኑበት ሁኔታ የስልጣናቸው መሠረት የሆነውን ኤፈርት ልዩ ተጠቃሚ አያደርጉትም የሚል የዋህ አይኖርም። ይህንን የሚል ካለ ለሩብ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሌለ ወይም አውቆ የጨፈነ ሊሆን ይችላል።

በምርጫ 97 ማግስት የተደራጀው ቡድን የተነሱ ቅሬታዎች ለማጣራት በሂደው እንቅስቃሴ የቅድሚያ ቅድሚያ ከሠጣቸው መካከል "ኤፈርትን" የተመለከተውን ነበር። ሆኖም በተለይም የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተሉ የህግ ባለሞያዎች ያቧቸው ሁለት ጥያቄዎች ተጣርተው ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ነበር። የህግ ባለሙያዎቹ "ኤፈርት በጎ አድራጎት (ኢንዶውመንት) በሚል አልተመዘገበም፣ ...ለምዝገባው አግባብነት ያለው ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ክፍል ኤፈርትን እንዳልመዘገበ አስታውቋል፣ የሚል ነበር። በሌላ በኩል የህግ ሙያተኞቹ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዴት እንደሚመዘገብ፣ ...የኢንዶውመንቱ ተግባር ምን መሆን እንዳለበት፣ ...በህግ ከተሠጣቸው ስልጣን ተላልፈው ቢገኙ እንዴት እንደሚቀጡና እንደሚሰረዙ አንቀጽ እየጠቀሱ አመላከቱ።

በነገራችን ላይ በአዲስ አበባ ከህዝቡ ጋር በየቀበሌው በተደረገው ውይይት እኔ ከ ጀነራል ('አቶ' 'ፕሬዝዳንት' 'አፈ-ጉባኤ') አባዱላ ገመዳ ጋር በአንድ መድረክ ላይ አብረን ተመድበን ነበር። ቦታው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 በሚገኘው አዳራሽ ነበር። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ የአካባቢው ነዋሪዎች የአቃቂ ጨርቃጨርቅ፣ ብረታ ብረትና ሌሎች ፋብሪካዎች የሚሠሩ ላብአደሮች ናቸው። መኖሪያ አካባቢው ፋብሪካዎቹ የተገነቡበት ስለሆነ እያንዳንዱን እንቅስቃሴና የመንግስት እርምጃ ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው።

በዚህም ምክንያት የነዋሪው ጥያቄ በሙሉ የኤፈርት ኩባንያዎች እና በአቃቂ ቃሊቲ የሚገኙ ነጋር ፋብሪካዎችን በማነፃፀር የሚቀርብ ነበር። በአብዛኛው በእልህ በተሞላ ስሜት የሚንተከተኩ ቁጭት የሚገልፀውን ንግግር እየሠሙ ለመቀመጥ አእምሮን ከአዳራሽ ውጭ ማስቀመጥ ይጠይቃል። ህወሓት አልመዳን ለማቋቋም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከንግድ ባንክ ወስዶ በሚንፈራገጥ ሠአት ከ7 ሺህ በላይ የአቃቂ ጨርቃጨርቅ ሠራተኞች ከስራ ተባረው ሜዳ ላይ ተጥለው ነበር። በወቅቱ በተፈጠረው መደናገጥ ራሳቸውን የገመድ ሲሳይ በማድረግ ያጠፉ ብዙ ናቸው። ብዙዎች ትዳራቸው ፈርሶ ቤተሰባቸው ተበትኗል። በርካቶች ተስፋ በመቁረጥ በከተማ ቢጋራ ራሳቸውን በመጥመድ ሞታቸውን አፋጥነዋል። ስራ አጥነት በፈጠረው ደንዛዛነት ከባባድ ወንጀሎችን ወደ መፈፀም የተሸጋገሩም ነበሩ። ከህጉ ውጭ የጦር መሳሪያ ዝውውርና ሽያጭ ጀምሮ ነብስ በመግደል ኪስ የማውለቅ ስራ በአከባቢው እየተለመደ ሔዶ ነበር። በፋብሪካዎቹ የነበሩ ድጋፍ የአካባቢው ወጣቶች በስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች የእግር ኳስ ጨዋታ የሚያዘወትሩ ትርቶ የደባል ሱስ ተጠቂዎች እንዲሆኑ ተደርጓል። ወትሮ በስራ ትጋትና የስራ ባህል ለ

ፋብሪካ ሠራተኞች ሀያ አራት ሠአት በፈረቃ ይሠሩ ነበር) የሚታወቁት ሠፆች የሞራል ስብራት ደባቸው ወደኋላ ተመልሠዋል። ተስፋ መቁረጥ በኢታቂ ኮሚኒል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

በቀበሌው አዳራሽ እኔና አባዱላ የሠበሠብናቸው የኢታቂ ነዋሪዎች ስለ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ያላቸው መረጃ በራሱ የሚገርም ነበር። የአልመዳ የሠው ሀይል አስተዳደርና ሽያጭ ክፍል ሀላፊ እንኳን እንደ እነሱ ኢንፎርሜሽን ያለው አይመስለኝም። አልመዳ በ3 ቢሊዮን ብር ለጨማሪ ማስፋፊያ እየሠራ እንደሆነ ያውቃሉ። ...በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት አባላት "የፖሊስ ዩኒፎርም" እና "የወታደር ሬንጀር" ከአልመዳ እንዲገዛ (ብቸኛ አቅራቢ አልመዳ ስለተደረገ) መገደዳቸውን ያውቃሉ። ...አቶ መለስ ለአልመዳ በቀረፀለት ኢምፓወርመንት ፕላን መሠረት ከ40 ሺህ በላይ የትግራይ ተወላጆች በአልመዳ ጨርቃ ጨርቃ ቋሚ የስራ እድል እየተፈጠረ መሆኑን ያውቃሉ። ...በአልመዳ ተቀጥሮ የሚሠራ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ላብ አደር ከኢታቂ ጨርቃጨርቅ ተመሳሳይ ቦታ ከሚሠራው ጋር የወር ደሞዙና ጥቅማ ጥቅሙ ሲነጻጸር ከሁለት እስከ ሦስት እጥፍ እንደሚበልጥ ጠንቅቀው ያውቃሉ።...ሌላው ቀርቶ የአልመዳ ጨርቃጨርቅ ሠራተኛ ምን ያህል ሰወተት እና አመት በአል ልዩ ጭማሪ (ቦነስ) እንደሚሰጠው መረጃ አላቸው። አልመዳን በባይኖኩለር (ሪሞት ኮንትሮል) የሚቆጣጠሩት የኢታቂ ነዋሪዎች እስኪመስሉ ድረስ።

*(በነገራችን ላይ በግንቦት 2001 ዓ.ም. በአርባምንጭ ከተማ የግንቦት 20 በአልን በማስመልከት የአርባምንጭ ከተማ ነዋሪ ጋር ለአንድ ቀን ያደረኩት ውይይት ከኢታቂው ጋር በይዘትም በቁጭትም ተመሳሳይ ነበር። የአርባምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በታቀደ ሁኔታ እንዲቃጠል እና ከጥቅም ውጪ እንዲሆን በማድረግ ከ5 ሺህ በላይ ሠራተኛ እንዲፈናቀል ተደርጓል። የአርባምንጭን ከተማ ከተማ ያደረጋት ፋብሪካ በመዘጋቱ የከበሩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የሞት መንገድ ተያይዘዋል። ሆምት ብዙ እንደሚያወሩት ከሆነ እዋሳ ደም ጨርቃጨርቅም ተመሳሳይ እጣ ደርሶታል።...አልመዳ አለከለማ...ኢታቂ፣ አርባምንጭና አዋሳ ደም በሚያስተፉ ክንዉር እንዲመቱ ተደርጓል። "አልመዳ አለከለማ...ኢታቂ አስቴ ትድማ" የሚለውን ብሒል ለእያምስት አመታት ጀርባ አስኪተላ እዳምሔሔሁ። ጀነራል አባዱላም እንድገለ አዋቀ፣ ሌላ ጊዜ አንገቱን አያወዛውዝ አዳምጧል። የሰማሁ ንግግር እንጎት እንዳለው አረጋግጧል። የተፈጠረው ለድሎ እንደሚስተካከል ቃል ገብቷል።)*

የሆነው ሆኖ እኔ እና አባዱላ የኢቃቂ ሳናስደርጎን በጥሞና ሱናመሆኑ፡፡ ነገሩ እስኪያቅለሸልሸን ድረስ እስካፍንጫችን ነገሩን። የሚነግሩን ሁኔታውን እንደምንለውጥላቸው ተስፋ አድርገው ሳይሆን ከህወሓት እና ባለሟሎቹ ጋር ያላቸው ቅራኔ የማይታረቅ መሆኑን እንድናውቅላቸው መሆኑን ጨምረው ገለጡልን። እዚህ ላይ አንድ ነገር መሸሸግ የማይፈልገው እኔም ከመድረኩ ሳልወርድ ምንም ነገር የሚለውጥ እንደማይኖር አውቅ ነበር። አባዱላም ያውቃል ነበር።

ለማንኛውም የሁሉም መድረኮች ጥያቄና ቅሬታ በፈርጁ በፈርጁ ተጠናክሮ ከአቶ መለስ ጋር በቤተመንግስት ውይይት ከመደረጉ በፊት ሪፖርቱ ለአቶ በረከት ስምኦን ላከን። በወቅቱ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ሀላፊ የነበረው በረከት በኤፈርት ላይ የተነሱትን ከ200 በላይ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ሠረዛቸው። ለድርጅቱ የምናቀርበው ሪፖርትም እሱ በላከልን ላይ ብቻ ያጠነጠነ መሆን እንደሚገባ አስጠነቀቀን። ከቤተመንግስቱ ስብሰባ በፊት ለሁሉም ሚኒስትሮች በበረከት ታርሞ ተቀሽሮ የተዘጋጀውን ሪፖርት ላከንላቸው። የኤፈርት ጉዳይ ከጥያቄም፣ ከአስተያየትም ከመፍትሄ ሀሳብም እንዲወጣ ተደረገ።

እነሆ! የቤተመንግስቱ ስብሰባ ላይ ሁሉም ሚኒስትሮችና ሌሎች ባለስልጣናት ተገኙ። የተቀሸረውን ሪፖርት እንዲያቀርብ የተመረጠው ህላዌ ዮሴፍ በመህረቡ ከንፈርና ፊቱን እየለዋ አከርባቱን ተያያዘው። የመጀመሪያውን ሪፖርት ያጠናቀርነው እኔ እና ፀጋዬ ሐይለማሪያም በእምነታ አንገታችንን እየነቀነቀን ለህላዊ አብዮታዊ ድጋፋችንን አሳየን። ሌሎች ባለስልጣናት በተመሳሳይ አደረጉ። ይህም ሆኖ ህላዌ ዘገባውን ጨርሶ በውይይት ወቅት ተሠብሳቢ ባለስልጣናት እጃቸውን ቸብ በማድረግ ስለ ኤፈርት ያነሣሉ የሚል ተስፋ ሠንቄ ነበር። ለነገሩ እኔ ብቻ ሳልሆን የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ከንፍ አባላት በሙሉ በጉጉት ጠብቀን ነበር። እኛ ያላደረግነውን ሌሎች ያደርጉታል ብሎ መጠበቅ አድርባይነት ቢሆንም የተወሰኑ ሚኒስትሮች ከህሊናቸው ጋ እየተሞገቱም ቢሆን ያቀርቡታል ብለን አስበን ነበር።

ይሁን እንጂ የጠበቅነው ሳይሆን ሁሉም ሚኒስትርና ባለስልጣን የተናጋሪ በሚመስል መልኩ "ኤፈርት" የሚለውን ቃል በወቅቱ በተቃዋሚ ጎራ ነግሶ የነበረውን "ቅንጅት" የሚል ቃል የመጥራት ያህል ከባድ ሆነ። ውሾን ያነሳ ውሾ ነው እስኪመስል ድረስ እንደበቶች ተለጎሙ። እን

ሌሎቹ አንዳንድ ነጥቦች የተለየ ሀሳብ ያራመደው ጁነዲን ሳዶ ብቻ ነበር። የህወሓት ፕሮፓጋንዳ ብዙ ቢመታውም ሊገነዘበው ያልቻለው ምገደኛው ጁነዲን ሳዶ ከህላዊ አፍ ተቀብሎ፣

"እኔ በነበርኩበት መድረክ በኢንዶውመንት ኩባንያዎች ላይ በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ህዝቡ የድርጅቶችን ግብረ- ሠናይነት ይጠራጠራል። በአመራራቸው ዙሪያ ግልፅነት መቆጣጠር አልቻልንም። ኢኮኖሚውን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ የሚል ስጋት በህዝቡ ዘንድ አለ። ኢንዶውመንት ኩባንያዎቹ ዙሪያ ሠፊ የህዝብ ግኙኝነት መሠራት ይኖርበታል" በማለት ተናገረ። ጁነዲን ላይ ለመጨመር ይሁን ለተቃውሞ የሚኒስትር ግርማ ብሩ እጅ አስቀድሞ ተቀሰረ። የአዲስ አበባ ከንቲ አባላት ለተቃውሞ እንደሆነ ጠረጠርን።

አቶ መለስ ለማንም ምንም አይነት ምላሽ ሳይሠጥ ወደሌላኛው ሪፖርት እንዲሸጋገር ህላዌ በእጁ ምልከት ሠጠው!

የቤተመንግስቱ ድራማ በዚህ ተጠናቀቀ።

ኤፈርትን በተመለከተ የማይደፈር ቀይ መስመር ያለው በኢህአዴግ ባለስልጣናት ዙሪያ ብቻ አይደለም። ስርአቱን በሚቃወሙ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሆነ የፓርቲው አመራሮች ዘንድ ግልጽ ውይይት የለም። አብዛኛዎቹ የሚያስማማቸው የጋራ ነጥብ ቢኖራቸውም ወደ መሠረታዊ ጥያቄዎች ሲመጣ በአደባባይ የማይገልጽ ልዩነት ይስተዋላል። ርግጥም ይህ ልዩነት ወደ ፊትለፊት መጥቶ ውይይት ቢደረግበት የሚሠነጣጠቁ አሊያም የሚፈርሱ ድርጅቶች መኖራቸው አይቀርም። እንደ ፀሀፊው እምነት የመሠነጣጠቁ እጣ ፋንታ ከሚደርስባቸው የተቃዋሚ ፖርቲዎች ግንባር ቀደም ሊሆን የሚችለው በሀገር ቤት "በህጋዊ መንገድ" የሚንቀሳቀሰው "መድረክ" መሆኑ አይቀርም።

የሰይጣን ጆሮ አይስማው'ና!

አብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲዎቹ እና አመራሮቹ በጋራ ከሚስማሙባቸው ነጥቦች መካከል ዋነኛው ህወሓት እነዚህን ኩባንያዎች ያቋቋመው በጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ህዝብ የተዘረፉ ንብረቶች ናቸው የሚለው ከሁቅ የራቀ ንብረቶች መሆኑ፤ ህወሓት ኩባንያዎቹ የትግራይ ህዝብ ንብረቶች ናቸው የሚለው ከሁቅ የራቀ መሆኑ፣ ኩባንያዎቹ ኢኮኖሚ ለመቆጣጠርና ነፃ ገበያ ስርአት እንዳይኖር በማሠብ እንደሆነ የጋራ ህሳቦች ናቸው። በተለይም የኩባንያዎቹ የሀብት ምንጭ በትጥቅ ትግሉ ዘመን በደረሱበት ቦታ ሁሉ የመንግስት ንብረት መውረሳቸው፣ እማጽያን ሆነው ሲያበቁ በእነሱ ቁጥጥር ስር ባዋሏቸ

...ራቶች ላይ የመንግስት ቁመና በመያዝ ግዳጅ እየጣሉ ሀብት ሲያሰባስቡ መኖራቸው፣..ህዝቡን በዛ ጉልበትና ማቴሪያል መዋጮ ኮታ በመጣል እየሰበሰቡ መሔዳቸው፣..ከውጭ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለህዝቡ (በተለይ በድርቁ ወቅት) የሚበረከቱ የገንዘብና የማቴሪያል እርዳታ ወደራሳቸው ካዝና መከተታቸው፣..አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ የመንግስት ስልጣን በመጠቀም በተለያዩ መልኩ ሀብታቸውን ለማሳደግ ያደረጉት ጥረት እንደሆነ፣..በተለይም የመንግስት ድርጅቶችን በዱቤ በመግዛት፣ ከተገዙም በኋላ እዳውን ባለመክፈል የኢኮኖሚ አቅማቸውን እንዳጠናከሩ መግባባት አለ።

*(በሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ሪፖርተር ባወጣው ዜና የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ሳባ ኢንጂነሪንግ 11.4 ሚሊዮን ብር የመንግስት እዳውን ለመክፈል ፈቃደኛ እንዳልሆነ አስታውቋል። ሳባ ኢንጂነሪንግ በመንግስት ይዞታ ስር የነበረውን የአዲስ አበባ ጡብ ማምረቻ ፋብሪካ በዱቤ ከገዛ በኋላ እዳውን እንደማይከፍል ተናግሯል። እንደ ሪፖርተር ዘገባ ከሆነ ሳባ ኢንጂነሪንግ በገዛው ውል መሰረት ክፍያውን በወቅቱ ባለመክፈሉ መንግስት 11.4 ሚሊዮን ብር እንዲከፍል ሆኗል። ሳባ ኢንጂነሪንግ የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት የነበረውን አዲስ ጡብ በ1999 ዓ.ም. የገዛ ውል ተፈርሞ ነበር። በወቅቱ ሳባ ኢንጂነሪንግ የሽያጩን ዋጋ 35 በመቶ ብቻ ከፍሎ ፋብሪካውን ተረክቧል። ቀሪውን 14.9 ሚሊዮን ብር በአምስት አመት ውስጥ እንዲከፍል ሁኔታዎች የተመቻቹለት ቢሆንም ለመክፈል ፍቃደኛ አይደለም።*

*በነገራችን ላይ አዲስ ጡብ ፋብሪካ ያረፈበት መሬት ብቻ በወቅቱ የመሬት ዋጋ ሊሆን ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ነበር። ፋብሪካውን አፈራርሶ መሬቱ ተሸንሽና ቢሸጥ ደግሞ ከ120 ሚሊዮን ብር ያላነሰ እንደሚያወጣ የመሬት አስተዳደር ሪፖርት አቅርቦ ነበር።)*

ታዲያ ኩባንያዎችን በተመለከተ በተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆነ አመራሮቻቸው በገጽ "ተከድኖ እየበሰለ ያለው" ጥያቄ ምንድነው?...ይህ በግልጽ መመለስ ያለበት ግን ደግሞ በከፍተኛ ፍራቻ የማይገለጠው ቁምነገር "በእነዚህ ፋብሪካዎችና የንግድ ተቋማት የትግራይ ህዝብ ተጠቅሟል ወይ?፣ የትግራይ ህዝብ ጥቅም እያገኘ እንዳልሆነ ለምን ራሱ ምስክርነት አይሰጥም" የሚለው ሆኗል። ርግጥም መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው?...እውነት ትግራይ ለምታለች ወይ? ተጠቅማለች ወይ? -የሚሉት ጥያቄዎች ግልፅ ምላሽ የሚያገኙት ናቸው። እየተነገረ ያለው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በሁሉም ዘርፍ በሞኖፖሊ የያዘ ድርጅት ስለሆነ በፖለቲካ ፓርቲዎች

ወሰቡ ድርጅትም ሆነ በህዝቡ አይታ አጽማቸው መታወቅ ያኖርበታል። ህወሓት ኂሳ ኢኮኖሚ ስላይንት የፖለቲካ የበላይነት አይረጋገጥም የሚለውን ብሔል በለዘሀ ኩባንያዎች አማካኝነት እውን እያደረገ መሆኑ በገሀድ አየታየ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ መተቸበትና አጀንዳውን በሩቅ መመልከት ብዙ መንገድ አያስጉዝም። ህወሓትን በመሸንቆጥና በአደባባይ ድፍረቱ የሚታወቀው ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ሳይቀር በአንድ የግል መፅሔት ላይ **"የትግራይ ህዝብ ተጠቃሚ ነዉ ብለው ያስባሉ ወይ?" ተብሎ ሲጠየቅ "ይህንን መመለስ ያለበት የትግራይ ህዝብ ነው" በማለት ምላሽ** ሰጥቷል። ይሉ ምን ማለት ነው? ...በድፍረት ንግግሩ ከሚታወቀው ፕሮፌሰር መረራ የሚጠበቅ ነበር? ...አሁንም ድፍረት አይሁንብኝ እና ፕሮፌሰር መረራ እውነትን ስመግለጥ ለምን አልደፈረም?...

ግራም ነፈሰም ቀኝ በኢህአዴግ አባላትም ሆነ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ በኤፈርትና በትግራይ ህዝብ መካከል ያለውን ተዛምዶ ገለጥለጥ አድርጎ መነጋገር አስፈሪ ሆኗል። ከህወሓት ውጪ ያሉ ኢህአዴጎች ይፈራሉ! የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ይፈራሉ። የችግሩ ቀጥተኛ ገፈት ቀማሽ የሆኑት ነጋዴዎች ይፈራሉ። ምሁራኖች ይፈራሉ። ሲቪክ ማህበራት ይፈራሉ። ዩኒቨርሲቲዎች ይፈራሉ። ሁሉም ይፈራል። ይህንን ሀገር እየጠፉ ያለ ጉዳይ በአጀንዳ ይዘው አይነጋገሩም። በተለይም በተቃዋሚው ጎራ የተሠለፉ የትግራይ ተወላጅ አብሮአቸው ካለ ፍራቻውና ድንጉጥነቱ ይጨምራል። ይህም ሆኖ በተቃዋሚ መሪዎች ላይ የሚታየው የተበቃይነት ስሜት መሸፈን የሚቻል አይደለም። እስከሚገባኝ ድረስ ፕሮፌሰር መረራ "ይህንን መመለስ ያለበት የትግራይ ህዝብ ነው" በማለት ምላሽ ሲሠጥ ደስተኛ ሆኖ አይደለም። የትግራይ ህዝብ መጠቀምና አለመጠቀሙን ለምን በስሜ በለው ይነገረዋል እያለ ነው።...ፕሮፌሰር መረራ እየኳሰ ያለው የትግራይ ህዝብ የሠላ እንደበት ያላቸው ልጆች በላሉት ራሳቸው ይናገሩ እያለ ነው።...ደግሞ ፕሮፌሰር መረራን ሆኜ መናገር ባልችልም፤ በዚህ ንግግሩ በትግራይ ህዝብ ላይ ቅሬታ ማሳደሩ እና ልቡን ሞልቶ መናገር እንዳልቻለ ነው። ዘለግ አድርገን ብንመለከተው ደግሞ በዚህ የፕሮፌሰር መረራ አስተያየት ጉብሩ አስራት ሊደሠት ይችላል ወይ ተብሎ መጠየቅ ያስፈልግ ይሆናል። ትዕምት የትግራይ ህዝብን እንዳልጠቀመ፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥም እዚህ ግባ የሚባል ድርሻ እንደሌለው በሙሉ እምነት የሚናገረው ጉብሩ አስራት በመረራ መልስ የማይቀር ሁኔ ነው። በሌላ በኩል ጉብሩ አስራት "የትዕምት ኢኮኖሚ እምነት ነው። አይደለም በሀገሪቷ በኢህአዴግ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ እዚህ ግባ አይባልም" በማለት በመጽሀፉ ላይ ማስፈሩ ፕሮፌሰር መረራን ማስደሰቱ አይቀርም። ያም ሆነ ይህ ሁለቱ ከፍተኛ የመድረክ

አመራሮች በሀሳብ ሜዳ እና ሜዳ መፋለሚያቸው በድርጅት ደረጃ አቋም እንዳልወሰዱ የሚያመለክት ነው። ቢያንስ ግን ፕሮፌሰር መረራ "ኤፈርት በኢህአዴግ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ስፍራ ለምን ነው" በማለት የትግል ጓዱ ገብሩ አስራት ሲናገር ምን አስቦ እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። መቃዠብ እንደሚቻለው በኤፈርትና ትግራይ ህዝብ መካከል ያለው የጥቅም ግንኙነት ንግግር እንዳይደረግበት ከፍተኛ ፍራቻ አለ። ፍራቻው እየተጠናከረ ከሄደ ደግሞ እርስ በርስ መጠራጠርና በጠላትነት መመልከት ቀጣዩ ደረጃ መሆን አይቀርም።

በተመሳሳይ መንገድ ኤፈርት ከትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ) እና ማህበረ ረድኤት ትግራይ (ማረት) ጋር ያለው ግንኙነት አደባባይ ወጥቶ አይገለጥም። እነዚህ ሶስት አደረጃጀቶች እርስ በርስ እየተመጋገቡ የሀብት ክምችት እየፈጠሩና ጡንቻቸውን እያጎለበቱ ቢሄዱም ስለውስጥ ተግባራቸው በገዢው ፓርቲ አባላትም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ጉዳዩና ስለ አስፈፃሚዎች በግልፅ ተነስቶ ውይይት አይደረግበትም።...የኦሮሞ ልማት ማህበር (ኦልማ) ካዝናውን ሙጥጥ አድርጎ ለትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ) 117 ሚሊዮን ብር ሲለግስ የኦህዴድ አባላት እጃቸውን በአፋቸው ይዘው "ወቸው ጉድ!" እየተባባሉ እርስ በርስ ከመነጋገር ውጭ ትንፍሽ አላሉም።_የደቡብ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ልማት ማህበር (ደልማ) ውስጥ አድርጎ ለትልማ 110 ሚሊዮን ብር በነሐሴ 1994 ዓ.ም. ሲለግስ የደኢህዴን ካድሬዎች "ሐይለማርያም የስልጣን ማግኛ እጅ መንሻ ሠጠ!" በማለት ከማማት ውጪ ያደረጉት ነገር የለም።ለገንዘቡ ባለቤት ለሆነው ለደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብም አልነገሩትም። በጀት የሚያጸድቀውና የሚመድበው ምክርቤትም አላወቀም።

በህወሓት/ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ዘንድም ኤፈርት፣ ትልማ እና ማረት ተቀናጅተው የትግራይን ህዝብ ተጠቃሚ እያደረጉ ነው የሚለውን ውስጥ ለውስጥ ከመነጋገር ተሻግሮ ፊትለፊት ለማውጣት ድፍረት የለም። መረጃ የላቸውም እንዳይባል በርካታ የአለም ዓቀፍ ተቋማት በየጊዜው ሪፖርት የሚያወጡበት ነው። እነዚህን ሪፖርቶች አንብቦ በማይመረምርና ለፖለቲካ ስራው ግብአት የማይጠቀም የፖለቲካ ድርጅት ካለ ተልእኮውን እያወቅምና ራሱን መመርመር ይኖርበታል። የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኢፍትሐዊነት በሚታይ ሠአት ተነጋግሮ ማጋለጥና እንዲስተካከል ማድረግ ትልቅ ስራ ነው። እሳው ባለም የፖለቲካ ትርፍ ማስገኘቱ አይቀርም።

ለምሳሌ በመስከረም ወር 1992 ዓ.ም. አሜሪካኖች ያወጡት ሪፖርት በኢህአዴግ አባላትና በነፃው ፕሬስ ዘንድ ከፍተኛ ውይይት የጫረ ነበር። በወቅቱ አቶ መለስ "ህዝሉ ሰላሰን ገዝብ ብቻ ስጡን" በማለት የአለም አቀፍ እርዳታ ለጋሾችን የተናገሩበት ወቅት በመሆኑ የአሜሪካኖቹ ሪፖርት ልዩ ትኩረት አግኝቶ ነበር። በዛው ዓመት ከ7 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለአስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው የተገለጠበት ስለነበር የአቶ መለስ ገንዘቡን ብቻ ስጡን ማለት ሁሉንም ግራ አጋብቶ ነበር። በውስጠድርጅት የፓርቲ ስብሰባም የኢህአዴግ አባላትና ካድሬዎች በመሰረታዊ ድርጅትና ጥናት ሀዋሳት ጉዳዩን ተመልክተው ጥያቄ አንስተው ነበር። በወቅቱ የአሜሪካን የእርዳታ ድርጅት (USAID) ባወጣው ሪፖርት መሰረት ድርጅቱ በአመቱ ከ80 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጣ የእህል እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ይልካል። ታዲያ ከሚላከው እርዳታ ውስጥ ስልሳ ከመቶው ወደ ትግራይ ይሔዳል። በክልሉ "ምግብ ለስራ" እና "ሴፍቲኔት" ለተደራጁ የትግራይ ተወላጆች እንዲከፋፈል ይደረጋል። በምግብ ለስራ እና ሴፍቲኔት ተደራጅቶ በእርከን፣ መንገድ ንጣፍ ስራ፣ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ችግኝ ቅከላ ያልተሠማራ የትግራይ ተወላጅ የመጣውን እርዳታ መውሰድ አይችልም።

*(በንገራችን ላይ ገንዘቡን ብቻ ስጡን የሚለው የአቶ መለስ አባባል በትግራይ ክልል አመራሮችና ካድሬዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበት ስለነበር ብዙ ርቀት መጓዝ አልቻለም። የትግራይ ክልል ከሌላው ተለይቶ 60% የሚገኘውን እርዳታ በዝርዝር ፕሮጀክት አስቀድሞ ያስደገፈው በመሆኑ ቅሬታቸውን ማቅረባቸው ተገቢ ነበር። የአቶ መለስ አስተያየት ወደ ተግባር መመንዘር ያልቻለው በዚህ ምክንያት ነው። የአሜሪካኖቹን ሪፖርት ዝርዝር ማብራሪያ ማግኘት የፈለገ በኮንግረስ ላይብረሪ ማግኘት ይቻላል። የሚቻገን ስቴት ዩኒቨርሲቲ እና የአሜሪካን የእርዳታ ድርጅት በጋራ የተዘጋጀ USAID አፍሪካ ያደረገውን ድጋፍ የሚመረምር ሪፖርት ነው።)*

በተለያዩ ጊዜያቶች የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በሊመንበርነት በመሩና አቦሙ ካሉ ግለሰቦች መካከል መጽሀፍ የጻፉትንና በእጄ የሚገኙትን ለማገላበጥ ሞክሬያለሁ። ከእነዚህ ውስጥ ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል "ህይወቱ እና የፖለቲካ አርምጃዬ" ...ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ "ዳንዲ የነጋሶ መንገድ" ...ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና "የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ገዢና የህይወቴ አርምጃ"፣ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ "ዴሞክራሲና ሁለንተናዊ ልማት" ...እና ሌሎቹ አያሌው "መድሎት" ይገኙበታል። ከእነዚህ አመራሮች ውስጥ እፈርት ላይ ትኩረት ሠጥተው ሀሳባቸውን የገለጡት ብርሃኑ ነጋ እና ልደቱ አያሌው ብቻ ናቸው። ቀደም ባለው ክፍል እንደገለጽኩት ፕሮፌሰር መረራ

ከአንድ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቆይታ በኤፈርት ላይ በቀረበላቸው ጥያቄ [illegible] ምልከታቸውን አስቀምጠዋል። ከዚህ በተረፈ ኢንጂነር ሀይሉ እና ዶ/ር ነጋሶ ኤፈርትን በተመለከተ ይህ ነው ተብሎ ሊጠቀስላቸው የሚችል ቁምነገር ማግኘት አልቻሉም። ሁለቱ [illegible] ተቃዋሚ ፓርቲ ዋርካ የሆኑ አዛውንቶች "ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠር ፖለቲካውን ይቆጣጠራል" የሚለውን አለም አቀፋዊ ስምምነት ሳይረዱት ቀርተው አይመስለኝም።

ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል ከፖለቲካ አመራርነታቸው በተጓዳኝ በከፍተኛ ኢንቨስት[illegible] ንግድ እንቅስቃሴያቸው ከፖለቲካው ባሻገር ባሉ አደረጃጀቶች እንዲሳተፉ ያደረጋቸው [illegible] በተለይም በንግድ ምክር ቤቶች እና የፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በርካታ [illegible] እንዲታዘቡ ማድረጉ አይቀርም። ከትዝብቶቻቸው ውስጥም የህወሓት ኩባንያዎች እንቅስቃሴ[illegible] ለመቆጣጠር የሄዱበትን ርቀት በቀላሉ ማየት ይችላሉ። በአኔ እምነት ኢንጂነሩ [illegible] በተመለከተ ከልምዳቸው በመነሳት ራሱን በቻለ መድብል ይዳስሱታል ብዬ አስባለሁ። እንዲሁም የመጽሐፍ አዘጋጅ የኢህአዴግ ልሳን ከፋይ የነበረው "[illegible] ጋዜጣ" ባልደረባ የነበረው [illegible] አበበ በመሆኑ ከወዲሁ ጥርጣሬያቸውን ቢያነሱም መጽሐፉ እንደሚቀጥል መዘገቡ [illegible] የሚያጨልም አይደለም።

እንደ እውነቱ ከሆነ ከዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ብዙ ጠብቄ ነበር። ምክንያቶቹም ነበሩኝ፡ በእኔ በኩል የትምህርት ዝግጅታቸው በቀጥታ የሚያያዝ በመሆኑ የፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን ነጥለው የሚያዩበት ሁኔታ አይኖርም። በሌላ በኩል ዶ/ር ነጋሶ ህወሓት አዲስ አበባን ከመቆጣጠሩ በፊት ጀምሮ ከ10 አመታት በላይ በስርአቱ ውስጥ በከፍተኛ አመራርነት የ[illegible] በመሆናቸው ሁኔታውን በተሳታፊነት ያውቁታል። ...ዶ/ር ነጋሶ ህወሓት የትግራይ፣ ወሎ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ አዲስ አበባ፣ አምቦና የመሳሰሉት ከተሞችን ሲቆጣጠር በእጅ የገባውን የመንግስት ንብረት ሲወርስ ተመልክተዋል።...ዶ/ር ነጋሶ ኩራዝን ጨምሮ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ንብረቶች ሚ[illegible] ራዲዮ ፋና ሲወርስ በቅርበት ነበሩ። ...ዶ/ር ነጋሶ የሆቴሎቹን ህግ ባልተከተለ መንገድ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ህወሓት በረሃ በነበረ ሠአት መድሐኒት ለህዝቡ አከፋፍሏል በማለት [illegible] ሚሊዮን ብር በላይ ይከፈለው የሚለውን መመሪያ ተመልክተዋል።...ዶ/ር ነጋሶ የህወሓት [illegible] ሚኒስትር ሲሆኑ ኩባንያዎቹ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከንግድ ባንክ ተበድረው ሲያበድሩ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ለመንግስት መልሰው አበደሩ ሲባል በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ውስጥ ነበሩ።...

ዶ/ር ነጋሶ ህወሓት የፖለቲካ ስልጣንን በኢኮኖሚ አቅም ለማጠናከር የአገሪቱ የሕግ ስርአት ከሚፈቅደው ውጭ "ኢንዶውመንት" አደራጀሁ ሲል አጠገባቸው ነበሩ። የኢትዮጵያ ህዝብና ነፃው ፕሬስ "ኢንዶውመንቶች የተቋቋሙበትን የህግ መሠረት አሳዩን! ለመሆኑ ኦዲት ይደረጋሉ ወይ?፣ የኦዲት ወጤታቸው ለምን ይፋ አይደረግም?" የሚሉ ጥያቄዎች ሲያነሱ በማስታወቂያ ሚኒስትርነት በኋላም በርዕሠ-ብሔርነት ስልጣን ላይ ተቀምጠው ነበር። የአሮጌ ኢትዮጵያዊ ኢንቨስትመንት እና ንግድ ስኬት ሲነሳ ዘወትር የሚታወሱት የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ኩባንያ ባለቤት አቶ ገብረየስ ቤኛ በህወሓት ተጠልፈው ሲጣሉ እንደ አቦ ኩማ ደመቅሳ ገመድ ባያቀብሉም የቤኛ ልጅ ወድቆ ተመልክተዋል። አቶ ግርማ ብሩ በኢቲቪ እና ሬዲዮ ቀርቦ " የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ በሕገ-ወጥ እንቅስቃሴ ተሳትፏል" የሚል የፈጠራ ክስ ከአቶ መለሰ ተቀብለው ሲያስተጋባ ዶ/ር ነጋሶ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ነበሩ። ቢያንስ "የሸዋ ፊውዳል ጠባይ አለው" ያሉትን ሚኒስትር ግርማ ቤተመንግስት ጠርተው አቶ ገብረየስ አንገት ላይ ያጠለፈውን ሠይፍ እንዲያነሳ ምክር ቢጤ መለገስ ይችሉ ነበር። ይህን ባለማድረጋቸው ካራው ግዘማዙ የመግደል ስራውን ሰራ። አሮጌው ግርማ አሮጌው ገብረየስን የመስዋት በግ አደረገ፤ ከስልጣን መነሻው እንዲ ይሆን ማድረግ ነውና!

***

ወደ ሌላው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር ስንመለስ የኢዴፓ ሊቀመንበር የነበረው ልደቱ አያሌውን እናገኛለን። አቶ ልደቱ "መድሎት" ብሎ በሰየመው መጽሀፉ "ነፃ ገበያ እንዴትና እስከምን?" በሚለው ርዕስ ስር ስለ "ኢንዶውመንቶች" አንስቷል። አቶ ልደቱ የህወሓት ኩባንያዎች ከማለት ይልቅ "የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች" በማለት ይገልፃል። ልደቱ "የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች" የበለጠ አሳሳቢ በሆነ መንገድ ነፃ ገበያውን ችግር ላይ እንደጣሉት በተደጋጋሚ ያነሳል። እነዚህ ድርጅቶች የአገሪቱን ሕግም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች አዋጅ በጣሰ ሁኔታ መመስረታቸውን በገፅ 237 ላይ፣

"ሁለተኛውና የበለጠ አሳሳቢው የዚህ ችግር መገለጫ ኢህአዴግ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቆጣጠራቸው የንግድ ድርጅቶች ያሉት መሆኑ ነው። በነፃ-ገበያ ስርአት ውስጥ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የንግድ ድርጅቶች አቋቁሞ ለመነገድ የሚያስችለው ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት ሊኖረው አይችልም። በወቅቱ በአገሪቱ ሕግም የፖለቲካ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የንግድ ስራ ሊሰሩ እንደማይችሉ በግልፅ ተደንግጓል። ነገር

ግን ኢሀአዴግ የአገራቱን ህግ ለማንም ባልተገለፀ ዘዴ ሸውዶ ለማለፍ በመሞከር አንድን ድርጅት በሌላው ድርጅት ባለአክሲዮንነት ድርሻ በማድረግና በየድርጅቶቹ አንዳንድ የድርጅቱን የቦርድ አመራር አባላት የአክሲዮኖቹ የአክሲዮን ድርሻ ባለቤት በማድረግ ያስመዘገባቸው 69 አካባቢ ከፍተኛና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች አሉት" በማለት ይገልፃል።

"የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ህገ- ወጦች መሆናቸውን በገጽ 239 ላይ እንዲህ በማለት ያስረዳል፣

*"በአገሪቱ ሕግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በንግድ ስራ ላይ መሠማራት እንደማይችል በተከለከለበት አገርና በአገሪቱ ሕግ ኢንዶውመንት ማለት ለትርፍ የማይሰራ በጎ አድራጎት ድርጅት መሆኑ በግልጽ በተቀመጠበት ሁኔታ ኢህአዴግ በአሳማኝ ምክንያት ሳይሆን በድርቅና እነዚህን የንግድ ድርጅቶች በእጁ ይዞ እስከቀጠለ ድረስም የቱንም ያህል ሌሎች በጎ ነገሮችን ቢሠራ የሕዝቡን የተሟላ ልባዊ እምነት ሊያገኝ ይችላል ብሎ ማመን ያስቸግራል። ኢህአዴግ የስልጣን የበላይነቱን ተገን አድርጎ እንዲህ አይነት ተቋማዊ ሙስና እየፈፀመ ባለበት ሁኔታም አገሪቱ ውስጥ ሕግን ለማስከበርም ሆነ ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችል የሞራል የበላይነት ይኖረኛል ብሎ ማሰቡም ግብዝነት ነው።"*

አቶ ልደቱ በመድሎት መጽሐፉ "ኢንዶውመንቶቹ የህዝብ ናቸው" በሚለው አባባል አይስማማም። በህዝብ ስም የተመዘገቡ ድርጅቶች ስላልሆኑ ከህግ አንጻር የህዝብ ናቸው ለማለት የሚያስችል መሠረት እንደሌለ ይገልፃል። ሕዝቡ ከእነዚህ ድርጅቶች ምንም አይነት ጥቅም እንዳላገኘ በገጽ 238 ላይ፣

*"... ድርጅቶቹ የሕዝብ ናቸው የሚለው አባባልም እውነት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ድርጅቶች በተለዩ የፓርቲ ባለስልጣናት የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች የአክሲዮን ድርሻ እንጂ በሕዝብ ስም የተመዘገቡ ድርጅቶች ስላልሆኑ ከሕግ አንጻር ይህንን ለማለት የሚያስችል መሠረት የለም።...ህዝብ በእነዚህ ድርጅቶች መጠቀም ይቅርና ድርጅቶቹ እንዴትና ለማን ጥቅም እንደሚሰሩ የሚያውቀው ነገር የለም...*" በማለት ይገልጻል።

ልደቱ "ሕዝቡ አልተጠቀመም" ብሎ ሲል የትኛው ህዝብ (ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ወይም ሌላ) ይበል ወይንስ የኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም። ምንአልባት ኢንዶውመንቶቹን በኢህአዴግ ባለቤትነት ስለገለጣቸው ህዝብ የሚለውም የኢትዮጵያ እንደሆነ

መሆኑን ይገልፃል፡ ርግጥም ይህን ማለት ከፈለገ ግንባሩ በእነዚህ ድርጅቶች መጠቀም ያለበት ድርጅቶቹ እንዲኖሩ ለማን ጥቅም እንደሚሰሩ የሚያውቀው ነገር የለም ብሎ ማለቱ ስለነበር መግባት አይፈልግም። ከዝርና በመቶ በላይ የሚሆኑት ኢንዶውመንቶች በህወሓት እጅ በሆኑበት ጊዜ ሲታይ ግን ህገቢ ሊከበሩ ይችላል ብሎ የሚል ከሰ መሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር የሚጣላ ነው። ስለዚህ በኩል "ኢኮኖሚውን በመቆጣጠር ፖለቲካውን መቆጣጠር" የሚለው የጠነከረ ሆኖ ህወሓት በሚገባ የመጠቀምና ያለመጠቀም አጀንዳው ወደ ትግራይ ህዝብ መወርወሩ ይገባዋል። ይህ ደግሞ ኢንዶውመንቶቹ በታሪካዊ አጋጣሚ የተፈጠሩ ሳይሆን ሆን ተብሎና ለፖለቲካዊ ጥቅምነት የተፈጠሩ ናቸው በማለት የቀረበው ሀሳብ ወደየትኛው ህዝብ ያነጣጠረ መሆኑ አመላካች ነው።

አቶ ልደቱ መንግስት መውሰድ ይገባዋል የሚለውን አስተያየት በመጽሐፉ አስፍሯል። ይህም በገጽ 240 ላይ፤

*"...ከዚያ በፊት በሕጉ በተቀመጠው መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በገበያ ውስጥ ተሳትፎ አይደረጉ የሚገኙ በገዥው ፓርቲ ተዘዋዋሪ ባለቤትነት የሚታወቁ የንግድ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ከገበያ ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።...* በማለት ይገልጻል።

ከዚህ አባባል መረዳት እንደሚቻለው አቶ ልደቱ የህወሓት/ ኢህአዴግ ኩባንያዎች ሙሉ ለሙሉ መክሠም እንደሚገባቸው የፀና እምነት አለው። ርግጥ በምን መልኩ ከገበያ ውጭ ሆነው መክሰም እንደሚችሉ በዝርዝር የተገለጠ ነገር ባለመኖሩ በሚወሰዱት እርምጃዎች ላይ ብዙ ማለት አይቻለም። ከዚህ በተጨማሪ ከንግድ ድርጅትነት ባሻገር ግዙፍ ኢንዱስትሪና ፋብሪካ የሆኑትን እንደ መሰቦ ሲሚንቶ፣ አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል፣ አድዋ መድሐኒት ፋብሪካ፣ ብሩክ ኬሚካል፣ ኢዛና ማዕድን...ወዘተ እንዴት ከገበያ ውጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በራሱ ግልጽ አይደለም። እነዚህ የኢንዶውመንት ካፒታሊዝም የሆኑ ተቋማት ህጋ-ወጥነታቸው ለከተረጋገጠ ድረስ፤...በሀገሪቷ ህግ መሠረት የፖለቲካ ድርጅቶችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች በንግድ ስራ እንደማይሳተፉ የተገለፀውን በጣሱበት ሁኔታ፤...የአገር ውስጥ እንቱ የተባሉ ብሔራዊ ከበርቴዎች ድርጅታቸውን በማፈራረስና በታቀደ መንገድ ለኪሳራ እንዲዳረጉ በማድረግ ራሳቸው በመቆጣጠር ሞኖፖሊ በፈጠሩበት ሁኔታ፤...የህወሓት የጓዳ ህልም የነበረውን "የኢኮኖሚ የበላይነት ለፖለቲካ የበላይነት" ፍልስፍና እውን በማድረግ የፖለቲካ ጡንቻ የፈጠሩ ተቋማት ከገበያ ውጭ ከማድረግ ባሻገር "ህጋዊ እርምጃ" እና "ይፋዊ ክስ" ቀርቦባቸው በፍትህ አደባባይ

መታየት እለባቸው የሚለው የብዙዎች አስተያየት ነው። የሦስተኛ አማራጭ መንገድ ትኩረት እንደሚያየው ግልጽ ባይሆንም!!

***

ወደሌላው ተቃዋሚ ድርጅት(ንቅናቄ) ሊ/መንበር ስንመለስ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እናገኛለን። የሚገርመኝ ነገር ሆኖ ከፕሮፌሰር ብርሃኑ ጋር ለተወሰኑ ቀናት በተናጥል የመገናኘት እድል አጋጥሞኛል። በሁለተኛው ማስታወሻ ዙሪያ የትኩረት ነጥቦቼን እንስቼ እሚውቸዋለሁ። ለወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል ሙያዊና ፖለቲካዊ ግምቱን እንዲነግረኝ ጠይቄዋለሁ። እውነት ለመናገር ከብርሃኑ ንግግሮች መገንዘብ የቻልኩት ነገር ቢኖር ከዛሬው ሁኔታ ካ የሚደርሰው "ማህበራዊ ቀውስ" በጣም ያሳሰበዋል። የኤፈርትን ጉዞም ከዚህ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ቀውስ ለይቶ እንደማያየው አስረግጦ ነግሮኛል። በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ ፈ እየሠደደ ከመጣው ሙስና አንፃር ግንባር ቀደሙን የሚይዙት እነዚህ ኩባንያዎች መሆናቸውን ይገነዘባል።

እንደ ብርሃኑ እምነት ከሆነ በየትኛውም የቀድሞ የኢትዮጵያ አገዛዞች እንደ አሁኑ ለይ ያወጣ የፖለቲካ ፓርቲ በግልጽ ባለቤትነት ተጠቅሞ የህገሪቷን ሀብት በሙሉ የሚዘርፍበት ኔትወርክ አልተዘረጋም። እነዚህ የህወሓት ኩባንያዎች የመንግስት ፖሊሲ አወጣጦች ላይ፣ ትላልቅ የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ፣ ከመንግስት የገንዘብ ተቋማት ብድር በመውሰድ ዙሪያ...ወዘተ ልዩ ተጠቃሚ በመሆን የሚፈፀም እንደሆነ ያስገነዝባል።...ብርሃኑ ኤፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች በህገሪቷ ማህበራዊ ቀውስ ያመጣሉ ብሎ ሲያስብ ከግዙፍነታቸውና ከሚያንቀሳቅሱት ከፒታል አንፃር በኢትዮጵያ የሚወዳደራቸው የግል ድርጅቶች አለመኖሩ ብቻ አይደለም። ኩባንያዎቹ ብሔረሰብ ተኮር (እሱ "ዘውግ ተኮር" ይላቸዋል) የፓርቲ ድርጅቶች መሆናቸው እጅግ አሳሳቢ እንደሆነ ይናገራል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም "አዳዲስ የትግራይ ባለሀብቶች" ከፓርቲው ጋር ባላቸው ትሥሥር አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ መፈጠሩ ትግሉን ውስብስብ እንደሚያደርገው እምነቱ ነው።

ለማንኛውምም ብርሃኑ እነዚህን የፓርቲ ኩባንያዎች "እባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ" በማለት የገለፀበትን አባባል "በዴሞክራሲና ሁለንተናዊ ልማት በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሀፉ አስፍሯል።

በዚህ መፅሀፍ "ያልተስተካከለ የመወዳደሪያ ሜዳና ኢትዮጵያ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅእኖ" በሚል ርዕስ ስር የሚከተለውን ይገልፃል፤

*"...ከዚህ ቀደም ሆኖ በሚያሳዩት መሰሉ በስልጣን ላይ ያለው የፖለቲካ ድርጅት በግልጽ ለሚያስተዳድራቸው የንግድ ድርጅቶች አማካይነት የመስኩን ዋናው ተጠቃሚ ለመሆን ነው። ከዚህ በፊት በነበሩት አገዛዞች ውስጥ ሆኖ የሚያውቀው አዲስና በተለይም የማይታወቅ ሜዳ በፍጹም ያልተስተካከለ የሚያደርገው ክስተት የገዢው ፓርቲ በቀጥታ በሁሉም የኢኮኖሚ መስኮች በመግባት ከተራው ጉጉዴ ግለሰብና ድርጅት ጋር የሚያደርገው "ውድድር" ነው። አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ እንደሚባለው የመንግስት ስልጣንን ያለምንም ተቃናቃኝ በብቸኝነት የሚቆጣጠረው ፓርቲና ከሞላ ጎደል በሁሉም የመንግስት የስልጣን እርከንም ሆነ ተቋማት የሚመደቡት የዚሁ ፓርቲ አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች በሆኑበት ሁኔታ እነኝህ የፓርቲ አባላት የመንግስት ስልጣናቸውን ተጠቅመው የራሳቸውን የንግድ ድርጅቶች መጥቀማቸው ምንም ጥያቄ የለውም፤...*

*"...ይህ ደግሞ ያለምንም ችግር ከመንግስት ባንኮች ብድር ከመውሰድ ጀምሮ በፕራይቬይታይዜሽን የመንግስት ንብረት የሆኑ ተቋማትን በርካሽ ዋጋ መግዛት፣ የመንግስት ጨረታ ያለምንም ተቃናቃኝ ማሸነፍ...ወዘተ በኢትዮጵያ በሠራው የሚታየው የዚህ አይነት መገለጫ ነው። በአንድ ወቅት የገዢው ፓርቲ መስራች አባት የሆነው አቶ ስብሃት ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ በሠጠው ቃለምልልስ በግልጽ እንደተናገረው እነኝህ የፓርቲ ድርጅቶች (በአንድ ወቅት የዚህ ግዙፍ የንግድ ኮንግሎመሬት ዋና አስተዳዳሪ ነበር) በአሁኑ ጊዜ በግዙፍነታቸውና በሚሳተፉበት የንግድ ዘርፍ ብዛት እንዲሁም በሚያንቀሳቅሱት ካፒታል መጠን ምንም የሚወዳደራቸው የሀገር ውስጥ የግል ድርጅቶች የሉም በማለት ይገልጻል።*

ሙሴናን ተሸከሞና ባህሪያዊ እድርጎ እንዲዳጎ፣ የተቃኘው ኤፈርት ለየት ያለ መገለጫ እንዳለው ብርሃኑ ደጋግሞ ገልፆታል። ኤፈርት የመንግስት ጨረታዎች፣ ግዢዎች፣ የኮንስትራክሽን ኮንትራቶች ህግን ባልተከተለ መንገድ በመውሰድ እንዲታብጥ የሆነው በማንአለብኝነት ከጀርባው ያሉናቸው ባለቤቶቹ ስብጥር በመሆኑ እንደሆነ ይገልጣል። በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ህወሓት አቅማ የተበከለ መሆኑን፤ እንዲሁም ከትግራይ የመጡ አዳዲስ ባለሀብቶች እየፈጠረ መሔዱን በዚህ ዘገባ ላይ፤

ግሎባል ድርጅቶች ውስጥ የወያኔ ድርጅት በዚህ መስክ እጅግ የተበከለው ከመሆኑ ባሻገር ከእነዚህ በባሰ ከሚታወቁ የወያኔ ድርጅቶች በተጨማሪ ድርጅቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከትግራይ የመጡ አዳዲስ ባለሃብቶችን በመፍጠርና በእነሱ ስር የድርጅቱን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ድርጅታዊ መሰናውን በግልጽ የሚያሳይ የስውር ቀለም ቀብቶታል። ይህ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን አያደር ማህበራዊ ቀውስን ሊፈጥር የሚችል አደገኛ የሙስና አዝማሚያ ነው" ይላል።

(ከብርሃኑ ነጋ ጋር በነበረን ተናጥላዊ ጨዋታ "የኢፈርት እጣ ፋንታ ምን ሊሆን ይችላል?" የሚል ጥያቄ አንስቼለት ነበር። በኢትዮጵያ ያለው መንግስት ተቀይሮ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሲመሰረት ብቻ መፍትሄ እንደሚያገኝ እምነቱ ነው። ዴሞክራሲያዊ ስርአት በፈጠርም ህወሓት ኢፈርትን ከትግራይ ህዝብ ጋር ለማያያዝ እየሰራ ያለው ስራ ችግሩን ውስብስብ ሊያደርገው እንደሚችል እምነቱ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የችግሩን ግልፅነትና ቀጣይነት ከወዲሁ መገንዘብ እንዳለባቸው ይገልጻል። በተለይ በስሙ እየተነገደ ያለውን የትግራይ ህዝብ የመፍትሄው አካል አድርጎ መውሰድ መታለፍ የሌለበት እንደሆነ ያስገነዝባል። ብርሃኑ በሊቀመንበርነት የሚመራው ንቅናቄ የሚፈልገው ግን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በኢትዮጵያ ተገንብቶ ማየት በመሆኑ በኢፈርትዎቹ ጉዳይ ላይ የፖሊሲ አጀንዳ እንዳልቀረፀ፤ ቀጣይ መንግስት ሆኖ መናገር እንደማይችል ጨምሮ አጫውቶኛል። በግለሰብ ደረጃም በንቅናቄው አቋም ተገዢ እንደሆነ አበክሮ ነግሮኛል።

በመጨረሻም የጋራ የሆነ ልጅ እንዲህ አለኝ!

"ለማንኛውም ችግር መፍትሄ ለማበጀት በመጀመሪያ ከግምት ማስገባት ያለብን የስራ ችግርን ለመፍታት የምንከተለውን አካሄድ ዘላቂ የሆነና ካሁኑም ችግር የባሰ መዘዝ ይዞ የማይመጣ መሆኑ በጥንቃቄ መመልከት ይገባናል። የዚህ አይነት የመፍትሄ አካሄድ ግቡ በሌላ ችግሩን ማስተላለፍ፤ ሲከፋ ደግሞ የከፋ ችግር ይዞ የሚመጣ ከሆነ በእርግጥም መፍትሄ ነው ለማለት ያስቸግራል። ሌላው ከግንዛቤ መወሰድ ያለበት ጉዳይ ማንኛውም መፍትሄ ከግምት የሚወስዳቸው ወይንም ማካተት ያለባቸው አንዳንዴ ተደጋጋፊ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተቃራኒ የሆኑ ጉዳዮች እንዳሉ ነው። ለምሳሌ በተቻለ መጠን የምናቀርበው መፍትሄ ችግሩን በተቀላጠፈ መንገድ የሚፈታ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ይህ ግን ብቻውን የመፍትሄውን ጥሩነት ለመመዘን በቂ አይደለም። በተለይ ማህበረሰቡን በሙሉ የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ መፍትሄው

የሚያስከፍለው እዳ ለሁሉም እኩል ነው ማለት አይደለም። ጉዳዩ የሠዎችን ተቃውሞ የሚመነዝር እስከሆነ ድረስና የተለያዩ ተቃዋሚ ያለበት ማህበረሰብ እስከሆነ ድረስ መቋቋሚያው የሚጠቀማቸውና በሚጎዳቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ውጤቱ የተለየ ሊሆን ይችላል። በዚህ ቅድም ያልኩትን ለመድገም እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በኢትዮጵያ መመስረት ለሁሉም እኩል የማህበረሰቡን ፕሮቶዎችና ችግሮች የመቋቋሚያው መሸጋገሪያ ብቻ ሳይሆን የመቋቋሚያው ዋና ቁልፍ ነው።")

ምዕራፍ **13**

# “የመንግስት የአንጃውን ቡድን!”

“ኤፈርት እኔ ከለቀቅሁ ወዲህ የጨመረው ፋብሪካ የለም። ለህብረተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍቻ የሚደረግ አስተዋጽኦም የለም።”

ስዬ አብርሃ

የቀድሞ መከላከያ ሚኒስትርና የኤፈርት ዋና ስራ አስፈጻሚ

“ግንባሯን ለመራር መሠረታዊ ስህተት ሊሆንት የሆነው የትዕምት ምርት በህወሓት/ኢህአዴግ ኢኮኖሚ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል ብሎ መገመቱ ነው።”

ገብሩ አስራት

የቀድሞ የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት

“ኤፈርት ሀገር ውስጥ አሉ ከሚባሉ ሀገራዊ ባለሃብቶች /ኮርፖሬሽኖች/ በሀብት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው፤ በኩባንያዎች ብዛትም በሀገሪቱ ስትራቴጂክ ሰርቪስ የሚሠጥ በመሆኑ አንድ ትልቅ የሀገር ሐይል ነው።”

ስብሀት ነጋ

ከአሜሪካ ድምጽ (ቪኦኤ) ጋር ያደረገው ቃለ-መጠይቅ

***

## ስብሀት ነጋ ምን አለ?

የሰኔ ወር የመጀመሪያው ሳምንት 2001 ዓ.ም....

ረፋዱ ላይ ገብረእግዚአብሄር የሚባለው የሚዲያ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት የእለቱን የሚዲያ ሞኒተሪንግ ይዞልኝ መጣ። ይህ ሰአት በሀገራችን እና በመላው አለም የተከሰቱ ጉልህ ክስተቶችን

የሚያመለክትበት ነበር። የሞኒተሪንግ ስራው ሀያ አራት ሰአት የሚሰራ ሲሆን ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጠው ነው።_

የሰጠኝን ወረቀት እያገላበጥኩ፣

"እሺ ገሬ! ምን አዲስ ነገር አለ? አገራችን አፍሪካና አለም እንዴት ውለው አደሩ?" አልኩት። ይህ የተለመደው አባባላችን ነው። የመላው አለም በሰላም ማደር ያሳጨንቀን ጀምሯል። ሮግ በሰላም ማደር ለኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ጥሩ ዜና አይደለም። ለነገሩ በሚዲያዎች አካባቢ ፀጥ ለ ነገር አይወደድም። ስራ እንደተሰራም አይቆጠርም።

እጆቹን ወደ ኪሱ እየከተተ፣

"በሰላም ነው ውለው ያደሩት። ኒዮ ሊብራሎቹም፣ ቆሞ ቀሮቹም፣ ተስፈኞቹም ሆነ ለማታዊ መንግስታቶች ደህና ናቸው። በሚዲያ ሞኒተሪንግ ካየናቸው ትልቅ ፕሮግራሞች የአበይ ስብሀት በአሜሪካን ድምጽ (ቪኦኤ) እንግዳ ሆኖ መቅረቡ ነው። አበይ ስብሀት እኮ የሙቀ ሰው ጥንቅላት ነው ያለው። አዲሱ አበበ የሚባለውን ኒዮሊብራል ጋዜጠኛ አፋን አዘጋው። የጋዜጠኛውን ኪራይ ሰብሳቢነት አጋልጦ ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳየ" አለኝ።

"ምን አልከኝ?" አልኩት ተደናግጬ። በፀጥታው ምክር ቤት አቶ መለስ የሰጡው ውሳኔ እያስታወስኩ። አቶ መለስ ከአሜሪካን ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም ሀላፊዎች ጋር ስምምነት እስከንደርስ ድረስ ማንም ባለስልጣን ወደ ሚዲያው እንዳይገባ አስጠንቅቋል።

ገሬ ቀጠለ፣

"አበይ ለቪኦኤ ጽቡቅ ቃለ መጠይቅ ሰጡ። የሚገርም ኢንተርቪው ነበር። ካሴት ይገፈልህ መጥቻለው። ስጋ ለዋትን ነው የምልህ አበይ ስብሀት ቁርጠኛ የትግራይ አባት ነው። ትዕምት በሆግ የትግራይ ህዝብ እንደሆነ ሳያወላዳ ተናግሯል። ኒዮሊብራሉ ጋዜጠኛ ትዕምት የህወሓት ነው እንዲሰው እንደፈለገ ከአጠያየቁ ያስታውቃል። በጣም አደገኛ ሰው ነው። አበይ ግን አልተበገረለትም። ከትዕምት አመራርነት የለቀቀው የተሻለ ብቃት ያላቸው ካድሬዎች በመኖራቸው እንደሆነ ሳይሸማቀቅ ተናግሯል። ኪራይ ሰብሳቢው ጋዜጠኛ በግድ ተገፍቼ ነው የወጣሁት እንዲሳው ፈልጉ ነበር። በዚህ ሳይወሰን ትዕምት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ባለሀብቶች በሀብት መጠን የመጀመሪያውን ደረጃ እንደያዘ ይቆ አድርጓል። ...እዚህ ጋር እንኳን ትንሽ ቅር ብሎኛል። በሀብት ብዛት አንደኛ ነው ባይል ጥሩ ነበር። አንተ ምን ይመስልሃል?" አለኝ።

መልስ ሳልሰጠው በመገረም ተመለከትኩት። ከኪሱ አውጥቶ የቀረፀውን ካሴት ሰጠኝ። የልቡ ኩራት የፈጠረው የልብ ምት ደረቱን ሰንጥቆ የሚወጣ ይመስል ነበር። ኮሪደሩ አስ ራስ ፀጉሩ የሚሰቅ ሆኖ ታየኝ። ገሬ የሊድዋ አንበሳ። እንግሊዝኛ በቅጡ ማንበብ የማይችሉ የውጭ ሚዲያዎች ሞኒተሪንግ ሀላፊ።

ለጠቅ አድርጎ፣

"መጀመሪያ ሞኒተር ያደረግነውን አንብበው። ቀጥለህ ካሴቱን ስማው። እርግጠኛ ነኝ እንደኔ ሙሉ ቀን ደስ ብሎህ ትውላለህ። ብጻይ በረከት ስምኦንም በአበይ ምላሽ የሚረካ ይመስለኛል" ብሎ አስተያየቱን ሰጥቶኝ ቢሮውን ጥሎ ሄደ።

የሰጠኝን ወረቀት ማንበብ ቀጠልኩ። ከወትሮው በተለየ ዶክመንቱ የቀረበ ነበረ። መጀመሪያ የጋዜጠኛ አዲሱ ጥያቄ ይቀርባል። አስከትሎ የስብሀት ነጋ ምላሽ ቃል በቃል ተገልብጧል። ወረቀቱን እያነበብኩ ሽመልስ ከማል መጣ። ኮፒ አድርጌ ሰጠሁት። ካሴቱን ቴፕ ውስጥ በመክተት አብረን ማዳመጥ ጀመርን።

ሽመልስ አዳምጦ ሲጨርስ፣

"እዚህ ጋር ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ ገፍቶ ያልሄደባቸው ቁምነገሮች ተመዝው ቢወጡ የአቶ ስብሀት ግጥጥ ያሉ ውሸቶች ፀሀይ ይሞቃቸው ነበር" በማለት ተናገረ።

"ምን ማለት ነው?"

ሽመልስ በቀይ ያሰመረበትን ወረቀት እያሳየኝ፣

"የመጀመሪያው ጥሬ ሀቅ ስብሀት ነጋ የቪኦኤ አዳማጭ አለመሆኑ ነው። አንድ ሰው አስተያየት እየሰጠበት ስላለው ሚዲያ አዳማጭ ሳይሆን እንዴት ትችት ሊያቀርብ ይችላል፣ ሽማግሌው በግልጽ እየተናገረ ያለው በሰሚ ሰሚ ያዳመጠውን ነበር። ይህንንም "...እኔ እዚህ እንደመጣው የሰማሁት ቪኦኤ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ሚዛናዊ አይደሉም፣ ሚናቸውን የሱ ናቸው፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች ካምፕ ነው የሚል ሰምቻለሁ። ...እኔ ከሰው ነው የምሰማው እንጂ አድማጭ አይደለሁም። ከሰው ስሰማ ግን ሚዛኑን የጠበቀ አይደለም ይላሉ። ወደ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያዘነብል ነው የሚል ሰምቻለሁ" በማለት ለመርዘኛው ጋዜጠኛ ነግሮታል አለኝ። ካሴቱን ወደኋላ መልሺ ሳዳምጠው ሽመልስ የታዘበው ትክክል ሆኖ አገኘሁት።

"እንግዲህ ከዚህ አባባል መረዳት የሚቻለው የሽማግሌው መንደር የወሬና አሉባልታ ለቃቃሚ መሆኑን ነው" አልኩት።

ሽመልስ አንገቱን እየነቀነቀ፣
"አይመስለኝም?" አለኝ።

"ታዲያ ምን ሊሆን ይችላል?" መልሼ ጠየኩት።

"ሽማግሌው ቀላል ሰው አይመስለኝም። የራስን ፍርድ ከመስጠት የሚመጣን ተጠያቂነት ለመሸሽ የወሰደው እርምጃ ነው"

መስማማቴን አሳየሁት፣
"ሊሆን ይችላል። ሌላ ምን ታዘብክ?" በማለት ጠየኩት።

ሽመልስ ወረቀቱን እያገላበጠ፣
"በሀገሪቷ ህግ መሰረት ህወሐትን በወንጀል የሚያስጠይቀው ነገር ተናግሯል። በቀድመው አዋጅ 46/ 1993 ሆነ በአዲሱ አዋጅ መሰረት የፓለቲካ ፓርቲዎች የንግድ ድርጅቶች ማቋቋም አይችሉም። እሱ ግን ህወሐት እንግሊዝ አገር የንግድ ድርጅት እሁንም አለው የሚል ምስክርነት ሰጥቷል" አለኝ።

ወረቀቱን እያነበብኩ፣
"ጋዜጠኛ አዲሉ ስብሀት ነጋ ከኤፈርት ለምን እንደተባረረ ጠይቆት ነበር። ስብሀትም ለመምራት የበለጠ ብቃት ያላቸውን ሰዎች እንመድባለን ተብሎ እንደሆነ ገልጿል። ከእኔ የበለጠ ብቃት አላቸው ያሏቸውን መዳቢው አካል መድቧል ብሏል" አልኩት።

ሽመልስ ጠቋሚ ጣቱን ወደ ቴፑ እያወዛወዘ፣
"እየሀ የዚህን ሽማግሌ ተንኮል። ሁሉንም ቃል በቃል ብናደምጠው ይሻላል" አለኝ።

ማዳመጥ ጀመርን፣

ለአዲሱ ጥያቄ ስብሀት የሚከተለውን ምላሽ ሰጠ፤

"ኤፈርት እንዳልከው እመራ ነበር። ለመምራት የበለጠ ብቃት ያላቸው ሰዎች እንመድባለን ተብሎ ነው። እና ከእኔ የበለጠ ብቃት አላቸው ያሏቸውን መዳቢው አካል መድቧል። ይኼ በማምግም የተደረሰበት ነው።"

አዲሱ እንዲህ በማለት ጠየቀ፤

"ወይዘሮ አዜብ መስፍን ( የአቶ መለስ ባለቤት) እንደሚመሩት ይነገራል። ልክነኝ?" በማለት ጠየቀው።

ስብሀት፣ "ትክክል አይደለም። ከአመራሩ አንዷ ናቸው።"

አዲሱ፣ "ኤፈርት ለመሆኑ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለው ይታወቃል? እዴት ተደርጎ ይታወቃል?" በማለት ጠየቀ፤

ሰብሀት እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጠ፤

"ኤፈርት ሀገር ውስጥ አሉ ከሚባሉት ሀገራዊ ባለሀብቶች/ ኮርፖሬሽኖች/ በሀብት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው። በኩባንያዎች ብዛትም በሀገሪቱ ስትራቴጂክ ሰርቪስ የሚሰጥ በመሆኑ አንድ ትልቅ የሀገር ሀይል ነው። የውስጥ ኦዲት አለው። ኩባንያዎቹ የውጭ ኦዲት እየተደረገ ለመንግስት ይቀርባል። ለፍትህ ሚኒስትርም ይቀርባል" አለው።

አዲሱ፣ "ኤፈርት ካፒታሉ ስንት እንደሆነ አልነገሩኝም?"

ስብሃት ነጋ ቀጠለ፣ "እንደገለጽኩት ኤፈርትን የሚያክል ካፒታል ያለው የሀገር ባለሀብት የለም።"

አዲሱ፣ "በአሀዝ ስንት ይሆናል?"

ስብሃት፣ "በአሀዝ ብዙ አላስታውስም። አስፈላጊም አይመስለኝም?"

አዲሱ ጥያቄውን እንዲህ በማለት ቀጠለ፤

"ኤፈርት የማነው?"

የሰብሃት ምላሽ፣

"በትግል ጊዜ የተጠራቀመ ገንዘብ ነው። የንግድ ድርጅቶችም ነበሩን። ማሽንማተን ቤቶች ነበረን። እንግሊዝ ቤት ነበረን። ሳዑዲ ሬስቶራንት ነበረን። መርከብም ነበረን። እንግዲህ ለገንዘብ ሚኒስቴር አንሰጠውም። የህወሓት ገንዘብ ነው። ለአያንዳንዳችንም ልንከፋፈለው አንችልም። የሁሉም የትግራይ ህዝብ ነው። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ሆኖ የሚገኘው ትርፍ ልማትን እንዲያስፋፋ የተወሰነ ካፒታል ነው..."

***

የሚዲያ ሞኒተሪንግ ከበረከት ስምኦን ጋር የምንሰራበት ሰአት ደረሰ። ከሽመልስ ጋር ተያይዘን ወደ ሁለተኛ ፎቅ ወደሚገኘዉ የበረከት ቢሮ ሔድን።

ጊዜ ሳላጠፋ የቪኦኤንና የሽማግሌውን ቆይታ ሪፖርት ማቅረብ ጀመርኩ። እንዲህ በማለት፣

"ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ በመጀመሪያ የጠየቀው በመንግስት ወይም በኢህአዴግና በቪኦኤ መካከል የግንኙነት መሻከር ለምን እንደተከሰተ ነበር፣ ስብሀትንም በልዩ ሁኔታ አመስግኖታል" አልኩት። በተለይ የመጨረሻዋ አርፍተ ነገር እንደምታስቆጣው ገምቻለሁ። ተመስገና የማያውቅ ሰው ሌላው ምስጋና ሲቀርብለት በሌላ መውሰዱ የተለመደ ነው። በረከት ከእቶ መለስ ውጭ ሌላ ሰው ሲመሰገን ደስ አይለውም።

እንደገመትኩት በረከት ፊቱን እያጉረጠረጠ፣

"ስብሀት በዚህ ጉዳይ ምን አገባው። ምን የሚያውቀውስ ነገር አለ?... ይሄ ሰው የሌለበትን መዘላበድ መቼ ነው የሚያቆመው? ...ለማንኛውም የጋዜጠኛውን ጥያቄ እና የስብሀትን መልስ አንብብልኝ" አለኝ።

የአዲሱን ጥያቄ እንደሚከተለው አነበብኩኝ፣

"የፓርቲ ውሳኔ ይሁን፣ የመንግስት ውሳኔ ይሁን አናውቅም። አንዳንድ የኢህአዴግ ዋና ዋና ሀላፊዎች ለቪኦኤ በተለይ ለአማርኛው ቋንቋ አገልግሎት ቃለ ምልልስ አንሰጥም የሚል አቋም ይዘው ነበር።እና በነገራችን ላይ እርሶ መጥተው ሁላችንንም አናግረው ዛሬ እርሶ ይህን ስለሰበሩልን እናመሰግናለን። ግን ያ! ውሳኔ ከየት የመጣ ነው? የሚል ነበር" አልኩት። አስከትቶም እቦይ ስብሀት ከቪኦኤ ጋር በተለይም ከአማርኛ ፕሮግራም ጋር ግንኙነት የለንም፣ ቃለ ምልልስም አናደርግም፣

እንነጋገርም የሚል ውሳኔ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ሆነ እንደ መንግስት የተወሰነ ነገር የለም፡ ማለቴን ጨምሬ ተናገርኩ።

በረከት አፍንጫውን እየነተተ፣

"ይሄ ሽማግሌ ምንድነው የሚቀባጠረው? ...ውሳኔው ላይ ሙቼ ነበር? ለምን የድርጅቱን መመሪያ ይጥሳል? አሁን ለመለስ እነግረዋለሁ" አለን። ወደ ነጩ ስልክ እጁን ሰዶ ቁጥሩን መጫን ጀመረ። ምን እንዳሳሰበው አላውቅም መልሶ ተወው።

*(በረከት አውነቱን ነበር። ከአሜሪካን ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም ጋር በተያያዘ በአቶ መለስ ጥብቅ ትእዛዝ ማንኛውም የመንግስት ባለስልጣን ለአማርኛው ፕሮግራም መግለጫ እንዳይሰጥ ታዞ ነበር። በአዲስ አበባ የሚገኙ የቪኦኤ የአማርኛ ፕሮግራም ጋዜጠኞችም ፍቃዳቸው ተነጥቆ ነበር። በአቶ በረከት ስምአን አዘጋጅነት በቪኦኤ ሊቀርቡ የሚገባቸውና የማይገባቸው ዝርዝሮች ተለይተው ለድርድር መነሻ ቀርበው ነበር። ኤ፤ቢ፤ሲ፤ዲ የሚል ደረጃ ወጥቶላቸው፡ የቪኦኤ አማርኛው ክፍል ጋዜጠኛ ሲቀጥር፣ ወደ ኢትዮጵያ ወኪል ሲልክ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት የሚያመላክት ዶክመንት ተዘጋጀ። በስራ ላይ ያሉት የቪኦኤ ጋዜጠኞች ተቃዋሚ፣ መሀል ሰፋሪ፣ ደጋፊና አቋሙ የማይታወቅ በሚል በአራት ጎራ እንዲከፈሉ ተደረገ። የትኛው ባለስልጣን ማንን ማግኘት እንዳለበት አቅጣጫ ተቀመጠ።... እንደ አውነቱ ከሆነ ቪኦኤ የአማርኛው መገናኛ አስጨናቂ ነበር። በጊዜውና በሰአቱ በሌላ ማስታወሻ ራሱን ችሎ ይቀርባል። ...ቪኦኤ ...ምአባቱ አውነት!!")*

የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራችን አልተጠናቀቀም። የዛሬው ትኩረታችን ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ሽማግሌው ስብሃት ላይ ሆኗል። ሽማግሌው በሰጠው ቃለ-መጠይቅ ላይ የኢህአዴግ የድሮ መርሆ የነበረውና የቀረውን ማንሳቱ ትክክል እንዳልሆነ ተናገርኩኝ። የቀድሞው መርሆ ላይ የኢህአዴግ ስኬት ራሱን በልቶ በመጨረስ መከሰም ነው ይል ነበር።

በረከት በድጋሚ እየተወራጨ፣

"እስቲ ይሔ ቀጥቀር የተናገረውን አንብብልኝ" አለኝ።

ስብሃት የተናገረውን እንደሚከተለው አነበብኩለት፣

"የኢህአዴግ አላማ የተሟጠነ ካፒታሊስት ዴቨሎፕመንት ማምጣት ነው። ይህ ካፒታሊስት ዴቨሎፕመንት ከመጣ በኋላ ራሱን ያጠፋል። ኢህአዴግ የዚህ ስርአት ባለቤት አይደለም። ካፒታሊዝምን አሳድጎ እና ለሚመለከታቸው መደቦች አስረክቦ ይጠፋል። ስለዚህ የኢህአዴግ ዋነኛ አላማ እድሜ ማራዘም ሳይሆን ኢህአዴግን ማጥፋት ነው።_ ኢህአዴግ በረጅም ጊዜ ስልጣን ላይ ከቆየ ውጤት አላመጣም ማለት ነው። _የኢህአዴግ ውጤት የሚለካው ኢህአዴግን የሚተኩ ዋነኛ መደቦች ሲፈጠሩ ነው" የሚል ነበር።

በረከት ምንም ምላሽ ሳይሰጠን የቢሮውን ኖኪያ ስልክ አነሳ። ነጩ ስልክ በልዩ ሁኔታ የነገ እንደሆነ ስለምናውቅ እኔ እና ሽመልስ እርስ በራስ ተያየን። በዚህ ስልክ የሚደውለውም ሆነ የሚደወለው አቶ መለስ ብቻ ነው። በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚካሄደው የመረጃ ልውውጥም በአማርኛ ቋንቋ የሚካሄድ አይደለም። ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በትግርኛ ነው። ለአንድም ቀን በአማርኛ ሲነጋገሩ ሰምቼ አላውቅም።

በአቶ ለመለስና በረከት መካከል የሚካሄደው የስልክ ወሬ በመራዘሙ ምክንያት እኔና ሽመልስ ወደ ኮሪደር ወጣን። ሽሜ ሲጋራውን እየለኮሰ፣

"ቅድም ያልከው አልገባኝም። ኢህአዴግ ስኬት ራሱን በራሱ በልቶ መጨረስ ነው ብሎ ያምን ነበር እንዴ?" በማለት ጠየቀኝ።

በየጊዜው የሚለዋወጡትን የውስጠ ድርጅት ሰነዶች ለማስታወስ እየሞከርኩ ለማስረዳት ጥረት አደረኩኝ። የኢህአዴግ ካድሬዎች በዘመቻ መጋሳ አዳማ ኢንዶክትሪኔሽን ወቅት ያሰለጠናቸውን ሰነዶች አንድ በአንድ እየጠራሁ እንደሚከተለው አስረዳሁት

በመጀመሪያ በአዳማ የከፍተኛ አመራር ስልጠና (1999 ዓ.ም.) "ልማትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚል ሰነድ ላይ የተደረገ ውይይት ነበር። ይህ ሰነድ በግልጽ የአስተሳሰብ እድገት ከሰላሳ ሙሉ ለሙሉ የሚሸር ሆነ። ከሶስት መጥቷል በማለት ከሶስት አመት በፊት የተያዘውን አቋም አመት በፊት (እስከ 1997 ዓ.ም.) ድረስ የነበረው ርእዮተ አለም አቶ ስብሀት ነጋ እንደገለፀው "የኢህአዴግ ዋነኛ አላማ ኢህአዴግን ማጥፋት ነው" የሚል ነበር። ኢህአዴግ በሁለት መልኩ እንደሚጠፋ ተገለፀ። "የቆሰለው ጅብ ተረት" የሚል ባለ መቶ ገፅ የውስጠ ድርጅት ሰነድ ተዘጋጅቶ ስልጠና ተሰጠበት።

በማስከተልም በኢትዮጵያ ሚሌኒየም መጀመሪያ ላይ "የታሪክ መጨረሻና ዳግ እናሪው የኤስያ እድገት" በሚል ርእስ አቶ መለስ ያዘጋጀው ሰነድ ይፋ ሆነ። ከላይ እስከ ታች ያለው የኢህአዴግ ካድሬ በስልጠና ተጠመደ። የጽክሁምንቱ መሰረታዊ ቁምነገር ቀድሞ የነበረውን "አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሊብራል ዴሞክራሲ ሊደርስበት የሚችለውን ጫፍ በማድረስ ራሱን በራሱ በልቶ ይጨርሳል" የሚለውን አሳቤ የሚሰርዝ ነበር። በተለይም ፍራንሲስ ፉኩያማ የሚባል የጃፓን ትውልድ ያለው አሜሪካዊ ተመራማሪ "የታሪክ መጨረሻና የመጨረሻው ሰው" (The end of history and the last man) የሚለውን መጽሀፍ በከፍተኛ ሁኔታ የሚተችና የተሳሳተ ድምዳሜ እንደሆነ የሚያሳይ ነበር።

ፍራንሲስ ፉኩያም የሊብራሊዝም ርእዮተ አለም የመጨረሻው የእድገት ደረጃ መሆኑን ይደመድማል። አቶ መለስ የፍራንሲስን ድምዳሜ አምኖ በመቀበል አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሄዶ ሄዶ የሊብራል ዴሞክራሲ ጫፍ ያደርሰናል የሚል ስብከት በኢትዮጵያ ምድር ዘርቶ ነበር። የተዘራው ሳይሰበሰብ "ፍራንሲስና የኢትዮጵያ ስምንተኛ ሺህ ሰባኪ ቁሶች መጪውን ጊዜ በመተንበይ ተሳስተዋል፣ የሊብራሊዝም ርእዮተ አለም የመጨረሻ መዳረሻ አይደለም" የሚል" አስተምህሮ መለስ" ብቅ አለ።

ሽመልስ ከግል የሰጠሁትን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተምህሮ በጥሞና ካዳመጠኝ በኋላ፣

"ታዲያ ይሄ የተቸነከረና ቆሞ የቀረ ሽማግሌ አዲሱን አስተሳሰብ መገንዘብ ካልቻለ ለምን አይገለልም?" በማለት ጠየቀኝ። የሽመልስ የጥላቻ ምንጭ የበረከት መናደድ መሆኑ ገብቶኛል። በረከት ከተናደደ ሽመልስ የንዴቱን ምክንያት ባያውቀውም እንኳን ይበሳጫል። በረከት የተቆጣው ሰው ካለ ሽመልስ ሰውየው ላይ እራስ ነብር ይሆንበታል። በረከት የጠላው የጋዜጠኛና ጋዜጣ ካለ ሽመልስ እንደምንም ብሎ ከምድረገጽ ያጠፋዋል።

ሽመልስ የጠየቀኝን ለመመለስ በማሰብ፣

"ምን መሰለህ ሽሚ! በህወሓት ውስጥ በስልጣን ለመቆየት ክፊሊክ ቤተሰባዊና የጥቅም ኔትወርክ መዘርጋት አለብህ። ቦናፓርቲዝም የምንለው ይሄንን ነው። በዘረጋኸው ኔትወርክ ውስጥ የሠገሰክቻቸውን ሰዎች በቁልፍ የመንግስትና የድርጅት ስልጣኖች ላይ ማስቀመጥ መቻል አለብህ። ስብሃት ደግሞ በዚህ ሁኔታ እንደምሳሌ የሚነሳ ነው። እህቱ ቅዱሳን ነጋ፣ ባለቤቷ አሊቃ ፅጋዬ፣ የገቢዎች ሚኒስትር የነበረው ጌታቸው በላይ... ማንን ጠርቼ፣ ማንን ልተው" በማለት ተናገርኩ።

ሽመልስ በጥሞና ሲያዳምጡኝ ከቆየ በኋላ፣

"ሽማግሌው ከእጁ የማይለያቸውን እና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነባቸውን መጽሐፍት እንድተረጉመው በረከት በሚስጥር ሰጥቶኛል። ለአንተም ሳይነግርህ አይቀርም...ፀሐፊው በዩጎዝላቪያ ዘውዳዊ አገዛዙን ለመገርሰስ በተደረገው ትግል የቲቶ ታማኝ አገልጋይ የሆነ ወታደር የነበረው ነው። Miloran Djilas ይባላል" አለኝ።

በመስማማት አንገቴን ከላይ ወደታች እያንቀሳቀስኩ፣

"በረከት እንዳነበው ሰጥቶኝ ነበር። አዲስ መደብ The New Class እንዴት እንደሚፈጠር የሚያብራራበት ነው። የስርአት ለውጥ ሲመጣ ስልጣንን በመጠቀም በዘመድ አዝማድ፣ በስርቆትና በጥቅም በመተሳሰር ሀብት እንዴት ማካበት እንደሚቻል የሚያመለክት ነው። Normal life cannot sustain revolutionary attitudes for long የሚለው ጥቅሱ ተመችቶኛል" አልኩት።

ሽመልስ የሆነ ነገር ትዝ ብሎት፣

"ቤተሰብ ስትል በአዜብ መስፍንና ጌታቸው በላይ መካከል አለመግባባት ተፈጥሯል የሚባል ነገር እየተሰማ ነው። የሁለቱ አለምግባባት ብዙ ነገር ሊያበላሽ ይችላል። በመለስና ሽማግሌው መካከል መቃቃር ሊፈጠር ይችላል" በማለት ሲጋቱን ነገረኝ።

:

መረጃው በኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ በሰፊው እየተነገረ በመሆኑ አዲስ አልሆነብኝም። የኤፈርት ማርኬቲንግ ዳሬክተሩ ጓደኛዬ ታጋይ አተይ ታደለም በአልኮል ሰአት በብስጭት ነግሮኛል። ጌታቸው በላይ ከገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትርነት ተዘዋውሮ የኤፈርት ምክትል ስራ አስፈፃሚ ሲሆን ኤፈርትን እንደሚለውጥ የሁሉም እምነት ነበር። ከዋና ስራ አስፈፃሚዋ ወይዘሮ አዜብ ጋር በዘረኝነት የሚስተካከሉ ቢሆንም ጌታቸው "በእውቀት ላይ የተሞረከዘ ዘረኝነት" ስለሚያራምድ ህወሓት በሚፈልገው መንገድ ኩባንያውን ሊመራው ይችላል። ይሁን እንጂ እውቀት አልባዋ አዜብ ብዙ ርቀት እንደማታስኬደው በብዙዎች ዘንድ ግንዛቤ ተይዟል።

ሽመልስ የማስበውን ያወቀብኝ ይመስላል፣

"ህወሓቶች ጌታቸው በላይን "ትንሹ መለስ" የሚሉት ለምንድነው? ቀጣይ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል የሚባለው ምን ያህል እውነት ነው?" በማለት ጠየቀኝ።

ስለ ጌታቸው በላይ የማውቀውን ያህል ገለፃ ሰጠሁት። "ትንሹ መለስ" ገለፃዬን አድርጌ ሲጨ የሚከተለውን ይመስላል።

***

"ትንሹ መለስ"

ጌታቸው በላይ ይባላል። ህወሓቶች በምሁርነቱ እጅግ ከሚኮሩባቸው ካድሬዎች አንዱ ነበር። በአንድ ወቅት "ትንሹ መለስ" የሚል ስያሜ ሰጥተውት ነበር። ከሚኒስትርነቱ በተጨማሪ ፕና ዋና የሚባሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቦርድ ሰብሳቢ ነበር። ቴሌኮሙዩኒኬሽን ጨምሮ የመንግስት የፋይናንስና ኢንሹራንስ ተቋማት በእሱ ቁጥጥር ስር ወድቀው ነበር። የሽማግሌው ዘመድ ጌታቸው በላይ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር የሆነበት አንዱ ምክንያት ለኤፈርት የግምሩ ቀረጥ ቅናሹን እንዲያደርግ ነበር። ትላልቅ ማሽኖችንና መኪኖችን ያለቀረጥ እንዲገቡም ጭምር ያደርግ ነበር። ከህወሓት አልፎ ኢህአዴግ ቢሮም ተጠቃሚ ሆኗል። በተለይ በ1998 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ኢህአዴግ ቢሮ ብቻ ያለቀረጥ በርካታ መኪናዎች በላይ ከዱብይ አስገብቷል።

የጌታቸው እና የወይዘሮ አዜብ ፀብ የመጨረሻው ጫፍ የደረሰው ቢትየቁ የኤፈርት ስራ አስኪያጅ ከተሾሙች በኋላ ነው። አቶ መለስ የቀድሞውን ስራ አስኪያጅ (አባዲ ዘሙ) አንስቶ ወደ ሱዳን እንዲያባርር ካስደረጋቸው በኋላ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እምብርት የሆነውን ኤፈርት ቁንጮ ሆነች። እስከትላም በኤፈርት ውስጥ ተለጥጦ የተዘረጋውን የሽማግሌው የቤተሰብ ኔትዎርክ ለመበጣጠስ የራሷን መረብ ዘረጋች።

ባለቤቷ ለወይዘሮ አዜብ የቀረፀው የመጀመሪያ ስትራቴጂ ከበረሀ ጀምሮ የህወሓት ታጋዮች የነበሩትን ካድሬዎች ማቀፍ ነበር። ይህንንም ለማስፈፀም እንዲረዳት በኤፈርት ኩባንያዎች ውስጥ ያሉ ታጋዮች የራሳቸው አደረጃጀት እንዲኖራቸው አደረገ። እነሱን የሚያነሳሳ መልእክት እየቀረፀ በእሷ በኩል ማስተላለፍ ጀመረ። ከእነዚህ ውስጥ "ትዕምት የተቋቋመው ለእናንተ ታጋዮች ቢሆንም እነ ስብሀት እና አርከበ እቁባይ የቤተሰብ ካምፓኒ አድርገውታል፣ _አመራሩን የያዙት በሙሉ የሽማግሌው ስብሀት ጓደኞች እና የስጋ ዘመዶች ናቸው፣ ...ከፍተኛ አመራር ላይ የተቀመጡት ታጋይ ስላልሆኑ ለታጋዩ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ደንታ የላቸውም፣ _ትዕምት የዝርፊያ እና የብክነት ማእከል ሆኗል" ...ወዘተ የሚሉ ነበሩ።

እነዚህ መልእክቶች በታጋዩ ዘንድ ተቀባይነት አገኙ። በተፈጠረው አደረጃጀት ታጋዩቹ ሲሰበሰቡ የመጀመሪያ አጀንዳቸው ትዕምት ሆነ። በተቋሙ የሚሰሩ አመራሮች ለሒሳብ ይቅረቡ የሚል ጥያቄ በሰፊው መነሳት ጀመረ። ወይዘሮ አዜብ ይህን የታጋዩን ቅሬታ መሰረት በማድረግ የስብሀት የስጋ ዘመዶች የፈፀሙትን ዝርፊያ ይፋ ማድረግ ጀመረች። የመጀመሪያ ትኩረቷም ምክትሏ የሆነው ጌታቸው በላይ እና የጉና ስራ አስኪያጆች የነበሩትን መስፍን ታደሰ እና ሙሉአለም ብርሀኔ ላይ አደረገች። እነዚህን ሰዎች ትኩረት እንድታደርግ ያደረጋት መሰረታዊ ምክንያት የስብሀት ነጋ የቅርብ ዘመዶች ብቻ መሆናቸው አይደለም።ግለሰቦቹ በአቅም ደረጃም ኤፈርት ውስጥ ያሉ አመራሮች ያላቸው ችሎታ ተጨምቆ ቢደመር እንኳን የሁለቱን በተናጠል አያክልም። ሁለቱም የዩኒቨርሲቲ መምህራን የነበሩ ናቸው። ወይዘሮ አዜብም የሁለቱን ብቃት በተግባር አይታዋለች። ስለዚህ ጌታቸው እና ሙሉአለምን ከትዕምት ማባረር ጊዜ የሚሰጠው ሆኖ አላገኘችውም።

በነገራችን ላይ ሸማግሌው ስብሀት ነጋ ሙሉአለም ብርሀኔን እና ሌሎች ዘመዶቹን ተጠቅሞ ከፍተኛ ዝርፊያ ማካሄዱ አይደለም በህወሓት በኢህአዴግ ደረጃም ይታወቃል። መስፍን ታደሰ የትዕምት የፋይናንስ እና የጉና ስራአስኪያጅ በነበረ ሰአት በውጭ ማሽና ሲሚንቶ ሽያጭ ላይ ሰበታጅ በመፈፀም ቤተሰባዊ ካፒታሉን እንዲያድግ አድርጓል። የመጀመሪያው ስብሀት ነጋ የትዕምት ዋና ስራ አስፈጻሚ በነበረ ሰአት ኩባንያው ሀያ ሚሊዩን ብር አውጥቶ ከውጭ ሀገር የገዛው ብረትና ሌሎች የግንባታ ማቴሪያሎች ወደ ሀገር ውስጥ ሳይገቡ ወደ ሌላ ሀገር እንዲሸሹ ማድረጋቸው ነው። የተገዙት ብረት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ጠፍተዋል በማለት ከኤፈርት አካውንት እንዲሰረዝ ተደርጓል። ይህን ዝርፊያ በተመለከተ ገብሩ አስራት "ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሀፉ አስገራሚ ዝርፊያ በማለት በገጽ 201 ላይ እንደሚከተለው ጽፎታል፡

*"ትዕምት በቢሊዩኖች የሚገመት ካፒታል ባለቤት ቢሆንም፣ በበርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎች ቢሰማራም ሙያዊ ብቃት ያለውና በስነ ምግባር የታነፀ አመራር ባለማግኘቱ በተደጋጋሚ ለኪሳራ፣ ለብክነት እና ለዝርፊያ ተዳርጓል። ከትዕምት ጋር ከተያያዙት አስገራሚ ዝርፊያዎች አንዱ በ1993 ዓ.ም ጉና በተባለው የትዕምት የንግድ ክንፍ የታዘዘው አንድ መርከብ ሙሉ የተጫነ የግንባታ ብረት የት እንደደረሰ ሳይታወቅ መቅረቱ ነው። ይህ ከስድስት ሚሊዩን ብር በላይ ያወጣል ተብሎ የሚገመተውን ብረት የትኛው ውቅያኖስ ውስጥ እንደቀረና ለዚህም ማን ተጠያቂ እንደሆነ አይታወቅም" በማለት እስከአሁንም እንቆቅልሽ እንደሆነበት ይነግረናል።*

ብዙ ውስጥ ድርጅት ኔትወርክ እንዳለው የሚታመነው ገብሩ አስራት ብረቱን የዋጠውን ውቅያኖስ ሚውቅ መሳኑ በራሱ የሚገርም ነው። ቢያንስ በግዥ ሂደቱ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎችን መጠየቅ ይቻል ነበርና፤ ለማንኛውም የእንቆቅልሹ ፍቺ ያዘለው ታሪክ በከፊል የሚከተለውን ይመስላል፣

ህወሓት ለሁለት ከመሰንጠቁ ጥቂት ቀናት በፊት የትዕምት ስራ አስኪያጅ የነበረው ስብሀት ነጋ ወደ ተለያዩ ሀገሮች የማንባታ እቃ ለመግዛት ይንቀሳቀሳል። ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ዋጋ የብረት ግዢ እንዲፈፀም ከአንድ ካምፓኒ ጋር ይዋዋላል። ብረቱን ጭነው ይመጣሉ ከተባለ የመርከብ ድርጅት ጋር ይነጋገራል። በውሉ ሰአት አብረው የሔዱት ሙያተኞች የተገዛው እቃ ከፍተኛ ዋጋ ያለው በመሆኑ የማኸርው ውል ኤፍ ኦ ቢ ዴስትኔሽን (FOB destination) በሚባለው ስርአት ከመፈፀም ይልቅ ኤፍ.ኦ.ቢ ኦሪጅን (FOB Origin) እንዲሆን ይመክሩታል። በሁለቱ ስርአቶች መካከል ያለው ልዩነት የኋለኛው ግዥ ስርአት (FOB Origin) ገዥው ሸያጩ ከተከናወነበት ቦታ ጀምሮ ሀላፊነት የሚወስድበት ሁኔታ የሚፈጥር ነው። በዚህ መልኩ የሚፈፀም ውል እቃውን የገዛው አካል የትራንስፖርት እና ሌሎች ሀላፊነቶችን ይወስዳል። በጉዞ ሒደት እቃው ቢጠፋም ተጠያቂ የሚሆነው ገዥ እንጂ ሻጭ አይደለም። ይህን የተረዳው ስብሃት ነጋ ግዥውን በኤፍ.ኦ.ቢ ኦሪጅን ያደርጋል። እቃውን የጫነችው መርከብ ውቅያኖስ ሳትሻገር በዛው ትቀራለች።

***

ከሙሉአለም ብርሀኔ ጋር የተያያዘው ሌላ ዝርፊያ ከሲሚንቶ ጋር ተያይዞ የተነሳው ነው። የሙገር ሲምንቶ የቦርድ ሰብሳቢ የሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ስዩም መስፍን በቀጥታ ትእዛዝ ሙገር የሚያመርተውን ምርት እንዲቀንስ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት በሀገሪቱ ከፍተኛ የሲምንቶ እጥረት ይከሰታል። አቶ መለስ እና ስዩም መስፍን ይህን የሚያደርጉበት መሰረታዊ ምክንያት የህወሓት ንብረት የሆነው መሰቦ ሲምንቶ ፋብሪካ ምርቶች ገበያውን እንዲቆጣጠሩት እና በፈለጉት ዋጋ እንዲሸጡ ለማስቻል ነበር። የስርአቱ ቁንጮዎች የሆኑት እነ አቶ መለስ እና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እምብርት የሆነው ትዕምት ሲያጭበረብሩ የተመለከተው ሙሉአለም ለራሱም አልቦዘነም። የስዬ አብርሃን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም እንዳይል፤ የስዬ ጠባሳ ገና አልተገለጠም ነበር።

ሙሉአለም የሚዘርፍበትን ሁኔታ ሲያፈላልግ አንድ ጓደኛውን ያገኛል፡፡ጓደኛው ለረጅም ጊዜ ተከማችቶ እየዛገ ያለውን እና ንብረትነቱ የጉና የሆነ ላሜራ በግማሽ ዋጋ እንዲገዛው ያስማማል፡፡ በምትኩም 40ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ አየር ባየር እንዲወስድ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት በወራት ውስጥ ራሱን እና ጓደኛውን በሚሊየነር ጐራ እንዲሰለፉ ያደርጋል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ስብሀት ነጋ እና ሙሉአለም ብርሀኔ የተቀናጁበት ዝርፊያ እና የአየር በየር ንግድ በወሬ የሚነገር አይደለም፡፡ በህወሓት ፓሊት ቢሮም ሆነ በኤፈርት አመራሮች ዘንድ ለሰምንታት ግምገማ የተካሄደበት ነው፡፡ ፈጻሚዎቹም ድርጊቱን መፈፀማቸውን አምነዋል፡፡ ነገር ግን የህግ ተጠያቂነቱ ከመጣ እነሱ ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ሰው በራሽ የሲምንቶ እጥረት ያስከሰቱትም አብረው መጠየቅ እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተውበታል፡፡

***

ወደ ጌታቸው በላይ ስንመለስ ደግሞ አዜብ የወሰደችው እርምጃ ወደ እስር ከማምራቱ በፊት ሀገር ጥሎ ጠፋ፡፡ ህወሓት ከፋኛ ተደናገጠች፡፡

የስብሀት ወገብም ተሰበረ፡፡ በእሱ ያልተጠበቀ እርምጃ ምክንያት ሸማግሌው ስብሀት የወይዘሮ አዜብ መቀለጃ ሆነ፡፡ ባገኘችው አጋጣሚ አንገቱን ማስደፋት ስራዬ አድርጋ ተያያዘችው፡፡ በኤፈርት ውስጥ የዘረጋውን ኔትወርክ ለመበጣጠስ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላት፡፡ ተራ በተራ እየጠረገች አወጣቻቸው፡፡ አቅማቸው ካሷ በታች እንደሆነ እርግጠኛ የሆነችባቸው አንደ ታጋይ አተይ ታደለ አይነት ሰዎች ብቻ ተወች፡፡

ጌታቸው በላይን በተመለከተ በየጊዜው የሚጉላሉብኝን ጥያቄዎች ሳላነሳ መሄድ ልቤ አልፈቀደም፡፡ ይህ ሰው የህወሓት ገዥ መደብ አካል በመሆን የማእከላዊ ኮሚቴና ፓሊት ቢሮ አባል ነበር፡፡ በአቶ መለስ ካቢኔ ውስጥ በሁለት የተለያዩ ተቋማት ሚኒስትር በመሆን ተሳትፏል፡፡ የንግድ ኢምፓየር የመሰረተው ትዕምት ሁለተኛ ሰው ነበር፡፡ የዚህን ተቋም የዝርፊያ ስትራቴጂ ለማስፈፀም በግንባር ቀደምትነት የተንቀሳቀሰ ሰው ነው፡፡

ከህወሓት ለሁለት መሰንጠቅ በኋላ የህወሓት ካድሬዎች ስርአቱን ጠጋግኖ ከሚያስቀጥሉ ሰዎች ግንባር ቀደም አድርገው ይወስዱት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት "ጌቾ ከአዜብ እንጂ ከህወሓት